የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

፴፪ኛ ዓመት ቁጥር ፶፭
አዲስ አበባ ነሐሴ ፳፰ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

32th Year No. 55
ADDIS ABABA, 26th August, 2026

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፱/፪ሺ፲፰

የመረጃ ነጻነት አዋጅ.....ገጽ ፳፻፭

Content

Proclamation No. 1427/2026

Access to Information Proclamation.....

.....Page 20005

አዋጅ ቁጥር ፭፻፵፱/፪ሺ፲፰

የመረጃ ነጻነት ለመደንገግ የወጣ አዋጅ

ዓለም አቀፋዊ የመረጃ ነጻነት ጽንሰ ሐሳብ እድገት ደረጃን ግምት ውስጥ በማስገባት የሀገራችንን የመረጃ ነጻነት ሕግ ማዘመን አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የመረጃ ነጻነት እና መገናኛ ብዙኃንን የሚመለከቱ ድንጋጌዎች በአንድ አዋጅ መውጣታቸው የመረጃ ነጻነት ሕግ በተገቢ ዝርዝር ሁኔታ፣ በተሟላ የአስተዳደር ስርዓት እና በአፈጻጸም ግልጽነት እንዳይቀርብ በማድረጉ፤ ዘርፉ ከደረሰበት ያደጉ ሃሳቦች፤ ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶችና መግለጫዎች እንዲሁም ከቴክኖሎጂ እድገት ጋር በማጣጣም የመረጃ ነጻነት አዋጅ ራሱን አስችሎ ማውጣት በማስፈለጉ፤

PROCLAMATION No. 1427/2026

A PROCLAMATION TO PROVIDE FOR ACCESS TO INFORMATION

CONSIDERING, that Cognizing the International advancement of the concept of access to information, it has become necessary to modernize our country's Access to Information legislation;

WHEREAS, the enactment of provisions related to freedom of information and the media in a single Proclamation has prevented the freedom of information law from being presented with appropriate detail, a complete administrative system, and transparency in implementation; it has become necessary to enact a separate Freedom of Information Proclamation by aligning it with advanced global concepts in the sector, international human rights conventions and declarations, as well as technological progress;

ማንኛውም ሰው በመንግሥት ተቋም እና በግል ድርጅት እጅ የሚገኝ መረጃ የመጠየቅ፣ የማግኘትና የማሰራጨት ነጻነት ይበልጥ በማረጋገጥ ግልጽነትንና ተጠያቂነትን ለማስፈን በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፳፱ እና ኢትዮጵያ በተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠው የመረጃ ነጻነት ይበልጥ እውን ይሆን ዘንድ ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የመረጃ ነጻነት ሕግ አፈጻጸምን የመከታተል እና የመቆጣጠር ኃላፊነት የተሰጠው የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ሥልጣንና ተግባር ይበልጥ ለማጠናከርና በዝርዝር ለመደንገግ የሕጉን አፈጻጸም ማሳደግ በማስፈለጉ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚከተለው ታውጇል።

ክፍል አንድ
ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የመረጃ ነጻነት አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፬፻፳፯/፪ሺ፲፰" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

፪. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሐረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ፦

፩/ **"መረጃ"** ማለት በማናቸውም ዓይነት ቅርጽ የተቀናበረ ማንኛውም ሰነድ ሆኖ በቃል የሚሰጥ መረጃን ይጨምራል፤

RECOGNIZING, the need to establish a system to further ensure transparency and accountability by reinforcing the right of any person to seek, receive, and impart information held by public body and private organization, and to fully realize the access to information guaranteed under Article 29 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and international human rights conventions ratified by Ethiopia;

NOTING, the importance of strengthening and prescribing in detail the powers and duties of the Ethiopian Institution of the Ombudsman, which is responsible for monitoring and overseeing the implementation of Access to information law, in order to enhance its enforcement;

NOW THEREFORE, in accordance with Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

PART ONE
GENERAL PROVISIONS

1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Access to Information Proclamation No. 1427/2026".

2. Definition

Unless the context of the word or phrase indicates otherwise, in this proclamation:

1/ **"Information"** means any record, regardless of the form in which the information is organized and stored, and includes information given orally;

፪/ **"ሰነድ"** ማለት በማንኛውም ሰው በማንኛውም ጊዜ የተፈጠረ፣ የተቀዳ ወይም የተዘጋጀ ቢሆንም በመንግሥት አካል ወይም በግል ድርጅት እጅ የሚገኝ ሆኖ የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ/ ማንኛውም መዝገብ፣ ፋይል፣ በማሽን ወይም በእጅ የተጻፈ ጽሑፍ፤

ለ/ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የወጣ የመዝገብ ግልባጭ፤

ሐ/ የጎላ ቢሆንም ባይሆንም በማንኛውም ማይክሮ ፊልም ውስጥ ያለ ምስል ቅጂ፤

መ/ በኮምፒዩተር ወይም በሌላ በማንኛውም መሳሪያ ወይም ዘዴ በመታገዝ የሚታይ፣ የሚነበብ፣ የሚደመጥ ወይም የሚታወቅ መረጃ፤ ወይም

ሠ/ በማንኛውም አይነት ቅርጽ ወይም የማስተላለፊያ ዘዴ የሚገኝ ማንኛውንም መረጃ።

፫/ **"የመረጃ ኃላፊ"** ማለት ይህን አዋጅ እንዲያስፈጽም በመንግሥት አካል ወይም በግል ድርጅት የተመደበ ወይም የተሾመ ሰው ወይም ሌላ ኃላፊ ነው፤

፬/ **"የበላይ ኃላፊ"** ማለት የመንግሥት አካልን ወይም የግል ድርጅትን በበላይነት የሚመራ ሲሆን ምክትል ኃላፊን ያካትታል፤

፭/ **"ክፍያ"** ማለት እንዲሰጥ የተጠየቀ መረጃ በእጁ ለሚገኝ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት እንዲከፈል የተተመነና በመረጃ ጠያቂ የሚከፈል ገንዘብ ነው፤

2/ **"Record"** means anything created, recorded, or prepared by any person at any time and in the possession of a government body or private organization and includes the following:

a) any document, file, text written by machine or by hand;

b) an electronic record transcript;

c) a copy of an image in any microfilm, whether highlighted or not;

d) information that can be viewed, read, heard, or recognized with the aid of a computer or any other device or method; or

e) any information available in any form or medium.

3/ **"Information Officer"** means a person or other official designated or appointed by a public body or private organization to enforce this Proclamation;

4/ **"Head"** means the person who leads a government body or private organization in a superior position, and includes a deputy head;

5/ **"Fee"** means money estimated to be paid to a government body or private organization that has the requested information in its possession, and is paid by the information requester;

፮/ **"ክልል"** ማለት በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ መሰረት የተቋቋመ የመንግሥት መዋቅር ሲሆን ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፤

6/ **"Region"** means a government structure established in accordance with Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, and for the implementation of this Proclamation includes the Addis Ababa and Dire Dawa city administrations;

፯/ **"ሰው"** ማለት ተፈጥሯዊ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

7/ **"Person"** means a physical or juridical person;

፰/ **"የግል መረጃ"** ማለት ተለይቶ የሚታወቅ ግለሰብን የሚመለከት ሆኖ፦

8/ **"Personal Information"** means information about an identifiable individual, including, but not limited to:

ሀ) የግለሰቡን የውልደት፣ እድገት፣ ሞት፣ የህክምና፣ የትምህርት፣ የአካዳሚክ፣ የስራ አገልግሎት፣ የሙያ፣ የወንጀል ታሪክ ወይም ግለሰቡ ያደረገውን የንግድ ግንኙነት የሚመለከት መረጃ፤

a) information relating to the birth, growth, death, medical, educational, academic, employment history, professional, or criminal history of the individual, or information relating to business transactions in which the individual has been involved;

ለ) የግለሰቡን ብሄር፣ ማህበራዊ ምንጭ፣ እድሜ፣ እርግዝና፣ የጋብቻ ሁኔታ፣ ቀለም፣ አካላዊና አእምሯዊ ጤንነት፣ የጤና ብቃት ወይም ጉድለት፣ ሀይማኖት፣ እምነት፣ ባህል ወይም ቋንቋ የሚመለከት መረጃ፤

b) information relating to the ethnic, social origin, age, pregnancy, marital status, color, physical or mental health, well-being or disability, religion, belief, culture, or language of the individual;

ሐ) የግለሰቡን መለያ ቁጥር፣ ምልክት ወይም ሌላ መለያ፣ አድራሻ ወይም የደም አይነት የሚመለከት መረጃ፤

c) information relating to the identification number, symbol or other particular, address, or blood type of the individual;

መ) ስለሌላ ግለሰብ የማዕረግ እድገት፣ ሽልማት ወይም የገንዘብ ድጋፍ እንዲያገኝ በቀረበ ሀሳብ ላይ በሰጠው አስተያየት፣ አመለካከት ወይም አማራጭ ሀሳብ ውስጥ የማይካተት የግል አስተያየት፣ ሀሳብ ወይም ምርጫ የሚመለከት መረጃ፤

d) information relating to the personal opinions, views, or preferences of the individual, excluding views, opinions, or alternative proposals given by the individual regarding the promotion, award, or financial grant of another individual;

ሠ) የአስተያየት ሰጪው ስም የተሰረዘበትና ሶስተኛ ወገን የገንዘብ ድጋፍ፣ ሽልማት ወይም የማዕረግ እድገት እንዲያገኝ በቀረበ ሀሳብ ላይ ግለሰቡ የሰጠው የግል አስተያየት ወይም አማራጭ ሀሳብ የያዘ መረጃ፤

e) information containing the personal views or alternative proposals given by the individual regarding the financial grant, award, or promotion of a third party, where the name of the commenter has been redacted ;

ረ) ሌላ ሰው ስለግለሰቡ ያለውን አመለካከት ወይም የሰጠውን አስተያየት የያዘ መረጃ፤ ወይም

f) the views or opinions of another person about the individual; or

ሰ) የግለሰብን ስም የያዘ መረጃን ወይም መገለጹ በራሱ ግለሰባዊ መረጃን የመግለጽ ውጤት ሊያስከትል የሚችል መረጃ ያካትታል። ሆኖም ከሞተ ፳ አመት የሞላው ግለሰብን መረጃ አይጨምርም።

g) information that includes the name of the individual or information the disclosure of which would, in itself, result in the disclosure of personal information. However, it does not include information concerning an individual who has been deceased for 20 years.

፱/ **"የመንግሥት አካል"** ማለት በፌዴራል ወይም በክልል ሕገ መንግሥት ወይም በሌላ ሕግ መሰረት የተቋቋመ ወይም በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥታዊ መዋቅር ውስጥ በየትኛውም እርከን ላይ የሚገኝ ወይም በፌዴራል ወይም በክልል መንግሥታት የባለቤትነት ይዞታ ስር የሚገኝ ወይም ተጠሪነቱ ለፌዴራል ወይም ለክልል መንግሥት የሆነ ማንኛውም መንግስታዊ ተቋም ሲሆን የመንግሥት የልማት ድርጅትን ይጨምራል፤

9/ **"Public Body"** means any governmental institution established by the Federal or Regional Constitution or other laws, or existing at any level within the Federal or Regional government structure, or owned by or accountable to the Federal or Regional government, and includes public enterprises;

፲/ **"የግል ድርጅት"** ማለት በዚህ አዋጅ ለመንግሥት አካል በተሰጠ ትርጓሜ ውስጥ የማይሸፈን እና በመንግሥታዊ ስራ ላይ የተሰማራ ወይም መንግሥት የአክሲዮን ድርሻ ያለው የንግድ ማኅበር ነው፤

፲፩/ **"መንግሥታዊ ሥራ"** ማለት ከመንግሥት አካል በመወከል ፍቃድ መስጠትን እና መከልከልን ጨምሮ አስተዳደራዊ ተግባራትን እንዲሁም የትምህርት፣ የጤና፣ የትራንስፖርት፣ የባህል እና መሰል አገልግሎት ማከናወንን ያካትታል፤

፲፪ **"የገንዘብ ትስስር"** ማለት በማንኛውም ደረጃ ይሁን መጠን መንግስት በግል ድርጅት የንግድ ሥራ እቅስቃሴ ውስጥ የገንዘብ ወይም የአክሲዮን ድርሻ ያለው እንደሆነ ነው፤

፲፫/ **"ሦስተኛ ወገን"** ማለት ከመረጃ ጠያቂ ወይም መረጃ ከተጠየቀው የመንግስት አካል ወይም የግል ድርጅት ውጪ የሆነ ማንኛውም ሰው ነው፤

፲፬/ **"የሕዝብ ጥቅም"** ማለት ከግል የጥቅም ፍላጎት በላይ የማኅበረሰቡን የደኅንነት፣የምጣኔ ሃብት፣ የፖለቲካ እና መሰል ተፈጥሮ ያለው መብትና ጥቅም ጨምሮ የሰፊውን ሕዝብ ተጠቃሚነት የሚመለከት ነው፤

፲፭/ **"ተቋም ወይም ተቋሙ"** ማለት በአዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፵፪/፪ሺ፲፩ (እንደተሻሻለ) እንደገና የተቋቋመ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ነው፤

10/ **"Private Organization"** means a business organization not covered under the definition given to a Public Body in this Proclamation, and engaged in government function or which has financial-tie with a government body;

11/ **"Government Function"** means administrative activities, including the granting and withholding of permits on behalf of a government body, as well as providing education, health, transport, culture, and similar services;

12/ **"Financial Tie"** means a situation where the government, at any level or to any extent, holds a financial or shareholding interest in the business activities of a private organization;

13/ **"Third Party"** means any person other than the information requester or the public body or private organization from which information is requested;

14/ **"Public Interest"** means the benefit of the public, including the rights and interests of the community regarding security, economic, political, and similar matters, which outweighs individual interests;

15/ **"Institution" or "the Institution"** means the Ethiopian Institution of the Ombudsman re-established under Proclamation No. 1142/2019 (as amended);

፲፮/ **"ምክር ቤት"** ማለት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ነው፤

፲፯/ **"መገናኛ ብዙኃን"** ማለት በየጊዜው የሚወጣ ሕትመትን፣ የብሮድካስት አገልግሎት ወይም የበይነ መረብ መገናኛ ብዙኃንን በመጠቀም የዜና ወይም የፕሮግራም ወይም የዜና እና የፕሮግራም አገልግሎት ለሕዝብ ለማቅረብ የተቋቋመ ድርጅት ሲሆን የዜና አገልግሎት ድርጅትን ያጠቃልላል፤

፲፰/ **"ከባድ የሥነ ምግባር ጉድለት"** ማለት በሥራ ላይ ባሉ ሕጎች እና በሙያ የሥነ ምግባር ደንቦች ላይ የተመሰረቱ መርሆዎችን የሚጥስ ተግባር መፈጸም ነው፤

፲፱/ **"አስተዳደራዊ እርምጃ"** ማለት በዚህ አዋጅ የተደነገገን ግዴታ ባልተወጣ ወይም በጣሰ የበላይ ኃላፊ፣ የመረጃ ኃላፊ፣ የሥራ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ላይ በተቋሙ የሚተላለፍ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ወይም የአስተዳደር ቅጣት ነው፤

፳/ በዚህ አዋጅ ውስጥ በወንድ ጾታ የተደነገገው የሴትንም ጾታ ያካትታል፡፡

፫. <u>የተፈጻሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል፦

፩/ በማንኛውም ጊዜና ሰው በተዘጋጀ፣ በተፈጠረ ወይም በተከሰተ በመንግሥት አካል ወይም በግል ድርጅት እጅ በሚገኝ መረጃ ወይም ሰነድ፤

16/ **"House"** means the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

17/ **"Mass Media"** means an organization established to provide news or programs, or both news and programs, to the public through periodical publications, broadcasting services, or online media, and includes news agencies;

18/ **"Grave Ethical Misconduct"** means committing an act that violates principles based on existing laws and professional codes of ethics;

19/ **"Administrative Measure"** means a written warning or an administrative penalty issued by the Institution against the head, information officer, official, or employee who has failed to fulfill or has violated the obligations provided under this Proclamation;

20/ Provisions of this Proclamation set out in the masculine Gender shall also apply to the feminine gender.

3. <u>Scope of Application</u>

This Proclamation shall apply to the following matters:

1/ Information or record in the possession of a public body or a private organization, regardless of when, or by whom, they were prepared, created, or originated;

፪/ በዚህ አዋጅ የተረጋገጠን መረጃ የመጠየቅ፣ የማግኘት፣ የማስተላለፍና መልሶ የመጠቀም ነጻነት በሚገድብ ወይም በሚጥስ ማንኛውም ሕግ፣ የአስተዳደር ውሳኔ ወይም አሰራር ላይ ነው።

2/ Any law, administrative decision, or practice that restricts or violates the freedom to request, receive, impart, and reuse information as guaranteed under this Proclamation.

፬. ዓላማ

4. Objective

የዚህ አዋጅ ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፦

The objectives of this Proclamation are as follows:

፩/ በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት እና በዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብት ስምምነቶች የተረጋገጠን የሰዎች መረጃና ሐሳብ የመጠየቅ፣ የማግኘትና የማስተላለፍ ነጻነት ተግባራዊ ማድረግ እና በመንግሥት አካልና በግል ድርጅት መከበሩን በማረጋገጥ የአሰራር ግልጽነት እንዲሰፍን ማስቻል፤

1/ To give effect to the right of persons to seek, receive, and impart information and ideas as guaranteed by the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and international and regional human rights conventions, and to ensure transparency of operations by ensuring that access to information is respected by public bodies and private organizations;

፪/ መረጃ ጠያቂ በፍጥነትና ሣይደክም በዝቅተኛ ወጪ ከመንግሥት አካልና ከግል ድርጅት መረጃ የሚያገኝበትን እና መረጃ በቀላሉ ለሕዝብ ተደራሽ የሚሆንበትን የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት፤ እና

2/ To establish a system through which an information requester can obtain information from public bodies and private organizations quickly, without hardship, and at a low cost, and to ensure information is easily accessible to the public; and

፫/ ስለመረጃ ነጻነት የተለያዩ አካላትንና ሕብረተሰቡን በማስተማርና በማሳወቅ የሕዝብ ተሣትፎንና ልዕልና ማረጋገጥ፤የአሰራር ግልጽነት፣ ተጠያቂነት፣ ውጤታማነት፣ ቅልጥፍና እና ፍትሐዊነት የሰፈነበት መልካም አስተዳደር ማጠናከር።

3/ To ensure public participation and supremacy by educating and informing various stakeholders and the community about access to information; and to strengthen good governance characterized by transparency, accountability, effectiveness, efficiency, and fairness.

፭. <u>መሠረታዊ መርሆዎች</u>

፩/ የዚህ አዋጅ ድንጋጌ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት፣ ከዓለም አቀፍና አህጉራዊ የሰብአዊ መብቶች ስምምነቶች እና ከዓለም አቀፍ የመረጃ ነጻነት መርሆዎች ጋር በተጣጣመ መልኩ መተርጎምና ተግባራዊ መደረግ አለበት።

፪/ ከኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት በስተቀር ይህ አዋጅ የመንግሥት አካልን ወይም የግል ድርጅትን መረጃ ይፋ ማድረግን በሚገድብ ወይም በሚከለክል በማንኛውም ሌላ ሕግ ወይም የአስተዳደር ውሳኔ ላይ ተቀዳሚነት አለው።

፫/ ይህ አዋጅ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት በዚህ አዋጅ ከተደነገገው ስርዓት ውጪ መረጃ የመስጠት ወይም አትሞ የማውጣት ኃላፊነት የሚገድብ ተደርጎ መተርጎም የለበትም።

፬/ ከመረጃ ነጻነት ጋር በተያያዘ ማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት ውሳኔ ወይም ድርጊት ሕጋዊ ወይም በዚህ አዋጅ ድንጋጌ አግባብ መሆኑን የማስረዳት ሸክም የመንግስት አካል ወይም የግል ድርጅት ነው።

5. <u>Fundamental Principles</u>

1/ The provisions of this Proclamation shall be interpreted and implemented in a manner consistent with the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, international and regional human rights conventions, and international principles of access to information;

2/ Except for the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, this Proclamation shall prevail over any other law or administrative decision that restricts or prohibits the disclosure of information by a public body or a private organization.

3/ This Proclamation shall not be interpreted as limiting the responsibility or authority of a public body or a private organization to provide or publish information through means other than the procedures established under this Proclamation.

4/ The burden of proof to show that any decision or act of a public body or a private organization regarding freedom of information is lawful or consistent with the provisions of this Proclamation shall rest upon the public body or the private organization.

ክፍል ሁለት

ስለመረጃ ነጻነት

፮. መረጃ ጠይቆ ማግኘት

፩/ በዚህ አዋጅ እንዳይገለጽ ከተከለከለ መረጃ ወይም ሰነድ በስተቀር ማንኛውም ሰው የግል መረጃውን ጨምሮ በመንግሥት አካል ወይም በግል ድርጅት እጅ የሚገኝ ማንኛውንም የመረጃ ዓይነት ወይም ሰነድ የመጠየቅ፣ የማግኘት፣ የማስተላለፍ እና መልሶ የመጠቀም ነጻነት አለው።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ነጻነት የተጠየው መረጃ ወይም የመረጃውን ምንጭ የያዘ ሰነድ በማንኛውም የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት እጅ የሚገኝ መሆኑን ጠይቆ የማወቅ እና በመንግሥት አካል ወይም በግል ድርጅት የሚገኝ መረጃ ወይም ሰነድ፦

ሀ) የመመልከት፣ ማስታወሻ የመውሰድ ወይም ጥቅስ የመገልበጥ፤

ለ) ትክክለኛ ግልባጭ የመውሰድ፤

ሐ) በማንኛውም ዓይነት የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ አማካኝነት ወይም ሰነዱ በኮምፒውተር ወይም በሌላ መሳሪያ የሚገኝ ከሆነም በዚሁ መሳሪያ ታትሞ የወጣ ቅጂ፤ ወይም

መ) በምስል፣ በድምጽ ወይም በሌላ ዘዴ የተቀመጠ ቅጂ የመውሰድ ነጻነትን ያካትታል።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌ በግል ድርጅት ላይ ተፈጻሚ የሚደረገው በግል ድርጅት እጅ የሚገኝ መረጃ መንግሥት ነክ ተግባርን ወይም የመንግሥት አካልን ድርሻ ወይም አክሲዮን የሚመለከት ከሆነ ነው።

PART TWO

ACCESS TO INFORMATION

6. Obtaing Information upon Request

1/ Except information or records that exempted under this proclamation, any person has the right to seek, receive, impart, and reuse any type of information or record in the possession of a public body or a private organization, including his own personal information.

2/ The right referred to under Sub-Article (1) of this Article includes the right to request and know whether the requested information or record containing the source of the information is in the possession of any public body or private organization, and the right to:

a) inspect, take notes, or copy extracts from a document or information;

b) obtain a certified copy;

c) obtain a copy via any type of electronic means or, if the document is stored in a computer or other device, obtain a printout from such device; or

d) obtain a copy stored in the form of images, audio, or through any other method.

3/ The provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall apply to a private organization only if the information in its possession concerns to governmental function or shareholding of a government body in the business organization.

፯. <u>የመረጃ ኃላፊ መመደብ</u>

፩/ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት የበላይ ኃላፊ ለዚህ አዋጅ ድንጋጌዎች ተግባራዊነትና አፈጻጸም ቀዳሚ ኃላፊነት አለበት፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የበላይ ኃላፊ ለመንግሥት አካል ወይም ለግል ድርጅት የሚቀርብን የመረጃ ጥያቄ ተቀብሎ የሚያስተናግድ እና በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ሌሎች ግዴታዎችን በኃላፊነት የሚወጣ እንደአስፈላጊነቱ አንድ ወይም ከአንድ በላይ የመረጃ ኃላፊ እና ባለሙያ መመደብ አለበት፡፡

፫/ የበላይ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የተመደበ የመረጃ ኃላፊ ለሥራው ብቁ እና ዝግጁ እንዲሆን ተገቢ ሥልጠና እንዲያገኝ ማመቻቸት፣ ለመረጃ ጠያቂ መረጃ መስጠት፣ የህዝብ ጥቅም መረጃ አትሞ ማውጣት እና በዚህ አዋጅ የተደነገጉ ሌሎች ግዴታዎችን መወጣት እንዲችል የተሟላ ሥልጣን እንዲኖረው የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

፬/ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት ኃላፊ፣ ሰራተኛ ወይም ባለሙያ ለመረጃ ኃላፊ ተግባር ወይም ሥራ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

፰. <u>የሰነድ አያያዝና አጠባበቅ ግዴታ</u>

፩/ ማንኛውም የመንግሥት አካል፦

ሀ) ትክክለኛ፣ የተረጋገጠ እና ጥቅም ላይ የሚውል መረጃ ወይም ሰነድ በአግባቡ የመያዝ፤ እና

7. <u>Designation of Information Officer</u>

1/ The head of a public body or a private organization shall have primary responsibility for the implementation and enforcement of the provisions of this Proclamation.

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the head shall designate one or more information officers and experts, as necessary, to receive and process information requests submitted to the public body or private organization and to fulfill other obligations stipulated under this Proclamation.

3/ The head shall have the duty to facilitate appropriate training for the designated information officer to ensure he is qualified and ready for the role, and to ensure the officer has full authority to provide information to requesters, publish public interest information, and fulfill other obligations provided under Sub-Article (2) this Proclamation.

4/ Any official, employee, or expert of a public body or private organization shall have the duty to cooperate with the information officer in the performance of their duties or functions.

8. <u>Duty of Records Management and Preservation</u>

1/ Every public body shall have the duty to:

a) properly maintain accurate, verified, and usable information or documents; and

ለ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው መሰረት የመረጃ ነጻነትን በሚያመቻች መንገድ በይዞታው ስር ያሉ ሁሉንም መረጃዎች ወይም ሰነዶች በአግባቡ ማደራጀትና የመጠበቅ ግዴታ አለበት፡፡

b) properly organize and preserve all information or documents under its possession in a manner that facilitates freedom of information as provided for in this Proclamation.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ የመንግሥት አካል፦

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, every public body shall:

ሀ) ፖሊሲውን፣ ውሳኔውን፣ አሠራሩን፣ መስተጋብሩን እና ሌሎች ተልዕኮውን ለማስፈጸም የሚያከናውናቸውን ተግባራት በበቂ ሁኔታ ለመመዝገብ የሚያስችሉ መዝገብ ማደራጀት እና መጠበቅ፤

a) organize and maintain records that sufficiently document its policies, decisions, procedures, interactions, and other activities performed to carry out its mission;

ለ) በኤሌክትሮኒክ መሣሪያ የተያዙትን ጨምሮ በይዞታው ሥር ያሉ መዝገቦች በሥርዓትና በመልካም ሁኔታ መያዛቸውን ማረጋገጥ፤

b) ensure that records under its possession, including those held electronically, are maintained in an orderly and proper condition;

ሐ) መዝገቦቹን እና የመረጃ አስተዳደር ስርዓቶቹን በኮምፒውተር ማዘመን፤ እና

c) computerize and modernize its records and information management systems; and

መ) የግል መረጃን ለማስተካከልና በቀላሉ ለማግኘት የሚያስችል አሰራር መዘርጋት አለበት፡፡

d) establish procedures that enable the correction of personal information and ensure it is easily accessible.

፫/ የግል ድርጅት በእጁ የሚገኝ መንግሥት ነክ ተግባርን ወይም የመንግሥትን የገንዘብ ወይም የአክሲዮን ድርሻ የሚመለከት መረጃ በየወቅቱ በአግባቡ አደራጅቶ መያዝ፣ መጠበቅ እና ማስተዳደር ይኖርበታል፡፡

3/ A private organization shall properly organize, preserve, and manage information in its possession if such information concerns governmental activities or government’s shareholdings in the business organization on a periodic basis.

፬/ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት መረጃው በመንግሥት አካሉ ወይም በግል ድርጅቱ ከተፈጠረበት ወይም በይዞታ ስር ከሆነበት ቀን ጀምሮ ለ፳፭ ዓመት መረጃውን ወይም ሰነዱን መያዝ አለበት። ሆኖም የ፳፭ ዓመት ጊዜ ገደብ ሲያበቃ መረጃው ወይም ሰነዱ በሕግ ሥልጣን ወደተሰጠው አካል ሊተላለፍ ይችላል።

4/ A public body or private organization shall retain the information or record for 25 years from the date the information was created by or came into the possession of the public body or private organization. However, upon the expiry of the 25 year period, the information or record may be transferred to the body legally authorized to receive such records.

፱. <u>አትሞ የማውጣት ግዴታ</u>

፩/ ማንኛውም የመንግሥት አካል በዚህ አዋጅ እንዳይገለጽ ከተከለከለ መረጃ በስተቀር የመንግሥት አካሉን የሚመለከት መረጃ በኤሌክትሮኒክስ ወይም በሌላ በመረጃ ማሰራጫ ዘዴ በተሟላ ሁኔታ አትሞ የማውጣትና ለጠቅላላው ሕዝብ ተደራሽ የማድረግ ግዴታ አለበት።

9. <u>Duty to Publish</u>

1/ Every public body, except for information or record exempted from disclosure under this Proclamation, shall have the duty to fully publish and make accessible to the public proactively information concerning the public body through electronic or any other communication methods.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚታተመው መረጃ የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ) ዋና መስሪያ ቤት ወይም ቅርንጫፍ የሚገኝበት አድራሻ፣ የፖስታና የኤሌክትሮኒክ መልዕክት አድራሻ፤ ስልክ ቁጥር፤

ለ) መዋቅር፣ ሥልጣንና ተግባር እና ለሕዝብ የሚሰጠው አገልግሎት ዝርዝር እና የኃላፊዎችን ማንነት፣ ሥልጣንና ኃላፊነት፤

ሐ) አገልግሎት ማግኛ ሂደትና ሥነ-ሥርዓት፣ ክፍያና የተቀመጠ የጊዜ ገደብ፤

መ) ሥልጣንና ተግባራቱ የሚመሩባቸው ፖሊሲዎች፣ አዋጆች፣ ደንቦች፣ መመሪያዎች፣ ማብራሪያ ሰነዶች እና ዝርዝራቸውን፤

2/ The information to be published pursuant to Sub-Article (1) shall include:

a) the address of the head office or branches, postal and electronic mail addresses, and telephone number;

b) organizational structure, powers and duties, a list of services provided to the public; and the identity, powers, and responsibilities of officials;

c) processes and procedures for obtaining services, including fees and established timelines;

d) policies, proclamations, regulations, directives, manuals, and other documents governing its powers and duties;

ሠ) በውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተፈጻሚ የሚሆነው ሥነ-ሥርዓት፣ የምክክር አካሄድና ሕዝብ በውሳኔ ላይ ስለሚኖረው ተሳትፎ፤

ረ) ተገልጋይ ጥያቄ ወይም ቅሬታ የሚያቀርብበት ሥነ-ሥርዓት እና አድራሻ፤

ሰ) በእጁ የሚገኝ መዝገብ ዓይነትና በመዝገቡ ውስጥ የሚገኝ መረጃ ዝርዝር፤

ሸ) መረጃ ለማግኘት የሚፈልግ ሰው የመረጃ ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት ዝርዝር ማብራሪያ፤ እና

ቀ) የመረጃ ኃላፊውን ስምና አድራሻ ያካትታል፡፡

e) procedures followed in decision-making, consultation processes, and public participation in decisions;

f) procedures and addresses for users to submit inquiries or complaints;

g) types of records held and the categories of information contained within those records;

h) a detailed explanation of the procedure for any person wishing to request information; and

i) the name and address of the Information Officer.

፫/ የመንግሥት አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ሥር የተመለከተውን መረጃ ቢያንስ በአመት አንድ ጊዜ አትሞ ማውጣት ይኖርበታል፡፡ ይሁንና መረጃው ታትሞ በወጣ በአንድ ዓመት ውስጥ በመረጃው ላይ የተደረገ ለውጥ ወይም አዲስ መረጃ ሲኖር ከሰላሳ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አትሞ ማውጣትና ለመረጃ ጠያቂ የሕትመቱን ቅጂ መስጠት ወይም እንዲመለከት ማድረግ አለበት፡፡

3/ A public body shall publish the information referred to in Sub-Article (2) of this Article at least once a year. However, if there are changes or new information within one year of publication, it must publish such updates within 21 days and provide copies of the publication to information requesters or make it available for inspection.

፬/ ማንኛውም የመንግሥት አካል፦

ሀ) በጀትን፣ ትክክለኛ ገቢና ወጪን፣ ገንዘብ ነክና የኦዲት ሰነድን፣ የድጎማ ተጠቃሚና አተገባበሩን እና ዝርዝር የግዢ አሰራርና ሂደት፤

4/ Every public body shall publish or notify the public within 30 days from the date the following public interest information is created or known:

a) budget, actual income and expenditure, financial and audit documents, subsidy beneficiaries and implementation, and detailed procurement procedures and processes;

ለ) የጨረታ ማመልከቻና ውጤት፣ ከማንኛውም አካል ጋር የሚደረግ የውል ስምምነት ቅጂ እና የውል አፈጻጸም ሪፖርት ሰነድ፤

b) tender applications and results, copies of contract agreements made with any party, and contract performance reports;

ሐ) አስተዳደራዊ እና ዳኝነት ነክ ውሳኔ ሲሰጥ ውሳኔውን እና የሃሳብ ልዩነት ካለም ልዩነቱን፤

c) administrative and judicial decisions, including the decision and any dissenting opinions;

መ) አጠቃላይ የሥራ የአፈጻጸም ሪፖርት እና በምክር ቤትም ሆነ በሌላ አካል የተሰጠ ግብረ መልስ፤

d) general performance reports and feedback provided by the Council or any other body;

ሠ) ማንኛውም የመንግስት ፕሮጀክት አፈጻጸም እና ውጤት መረጃ ወይም ፕሮጀክት ተግባራዊ ከመደረጉ በፊት ለጠቅላላው ሕዝብ ወይም ጥቅማቸው ለተነካባቸው ወይም ሊነካባቸው ለሚችሉ ወገኖች ከፕሮጀክቱ ጋር የተያያዙ ፍሬ ነገሮች መረጃ፤ ወይም

e) any information on the performance and outcome of a government project, or before implementing any project factual information related to the project to the public generally or to the persons affected or likely to be affected by the project; or

ረ) በግልጽነት እና በተጠያቂነት መርህ መሰረት ለሕዝብ ይፋ መደረግ የሚገባን ወይም የሕዝብ ጥቅም መረጃ ከተፈጠረበት ወይም ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ከ፴ ቀናት ባልበለጠ ጊዜ ውስጥ አትሞ ማውጣት ወይም ለሕዝብ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

f) Information that should be disclosed to the public based on the principles of transparency and accountability, or other public interest information.

፭/ የመንግሥት አካል በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ፊደል ተራ (ለ) የተጠቀሰውን ውል በሚፈጽምበት ጊዜ መረጃው የማይገለጽ ካልሆነ በስተቀር ስምምነቱን አትሞ የማውጣትና ለመረጃ ጠያቂ የመግለጽ ግዴታ እንዳለበት ለተዋዋዩ ወገን በማሳወቅ የስምምነቱ አካል ማድረግ አለበት፡፡

5/ When a public body enters into a contract mentioned in Sub-Article (4) Paragraph (b), it shall make it part of the agreement by notifying the contracting party that it has a duty to publish the agreement and disclose it to an information requester, unless the information is legally exempt from disclosure.

፲. የግል ድርጅት አትሞ የማውጣት ግዴታ

፩/ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ የሚሆንበት የግል ድርጅት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፮ መሰረት የመረጃ ጥያቄ ማቅረብ ሳያስፈልግ እንዲሁ ሊገኝ የሚችል የመረጃ አይነት ዝርዝር መግለጫ ወጥነት ባለው ጊዜ ቢያንስ በዓመት አንድ ጊዜ በኤሌክትሮኒክ ዘዴ አትሞ ማውጣትና ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይኖርበታል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በግል ድርጅት የሚታተመው መረጃ፡

ሀ) ድርጅቱ የሚገኝበትን አድራሻ፣ የፖስታና የኤሌክትሮኒክ መልዕክት አድራሻ፤ ስልክ ቁጥር፤

ለ) መመስረቻና መተዳደሪያ ደንብ፣ የመንግስት አካል ድርሻ፤

ሐ) የኃላፊዎች፣ የቦርድ፣ የኮሚቴዎች እና ሌሎች አካላት ማንነት፣ ስብጥር፣ተግባርና የሹመት ሂደት መግለጫ፤

መ) ለሕዝብ የሚሰጠው አገልግሎት ዝርዝር፣አገልግሎት ማግኛ ሥነ-ሥርዓት፣ የተቀመጠ የጊዜ ገደብ እና ክፍያ፤

ሠ) ዕቅድ፣ ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት፤ዓመታዊ በጀት፣ ገቢ፣ ወጪና ዕዳ ዝርዝር እና የኦዲት ሪፖርት፤

10. Duty of Private Organizations to Publish

1/ A private organization to which this Proclamation applies shall, at regular intervals and at least once a year, publish electronically and make available to the public a description of the types of information that can be obtained without the need to submit a formal information request under Article 6 of this Proclamation.

2/ The information published by a private organization pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall include:

a) the address where the organization is located, its postal and electronic mail addresses, and telephone number;

b) the Memorandum and Articles of Association, and the share of a government body;

c) the identity, composition, duties, and a description of the appointment process of officials, the board, committees, and other bodies;

d) a list of services provided to the public, procedures for obtaining the services, established timelines, and fees;

e) plans, plan performance reports, annual budget, details of income, expenditure, and debt, and audit reports;

ረ) የእያንዳንዱን ኃላፊና ሠራተኛ ዓመታዊ ክፍያ መጠን፣ ጥቅማ ጥቅም እና ስጦታ፤

f) the amount of annual salary, benefits, and gifts received by each official and employee;

ሰ) በግል ድርጅቱ ቁጥጥር ሥር የሚገኙ የመረጃ ምድቦች ዝርዝር፣ የመረጃ ጥያቄ አቀራረብ ሥርዓት ማብራሪያ፤ እና

g) a list of the categories of information under the control of the private organization, and an explanation of the procedure for submitting an information request; and

ሸ) የመረጃ ኃላፊ ስምና አድራሻ ያካትታል።

h) the name and address of the Information Officer.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም ተቋሙ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በግል ድርጅት የሚታተም ተጨማሪ የመረጃ ዝርዝር ሊወስን ይችላል።

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the Institution may, when it finds it necessary, determine additional categories of information to be published by a private organization.

ክፍል ሦስት

የማይገለጹ መረጃዎች

PART THREE

EXEMPTED INFORMATION

፲፩. የሦስተኛ ወገን የግል መረጃ

11. Personal Information of a Third Party

፩/ የተጠየቀው መረጃ ከሞተ ፳ ዓመት ያልሞላውን ሰው ጨምሮ የሦስተኛ ወገንን የግል መረጃ እንዲገለጽ የሚያደርግ ከሆነ የመረጃ ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ ይገባል።

1/ A request for information shall be refused if the disclosure of the requested information would involve the personal information of a third party, including an individual who has been deceased for less than 20 years.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም በሚከተለው ሁኔታ የመረጃ ጥያቄው ውድቅ መደረግ የለበትም፦

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a request for information shall not be refused under the following circumstances:

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ መሰረት ሦስተኛ ወገን የመረጃውን መገለጽ ካልተቃወመ ወይም መረጃው እንዲገለጽ ፈቃደኝነቱን በጽሁፍ ከገለጸ፤

a) If the third party does not object to the disclosure or has provided written consent for the disclosure of the information, pursuant to Article 14 of this Proclamation;

ለ) ሦስተኛ ወገን መረጃው በመንግሥት አካል ወይም በግል ድርጅት አማካኝነት ለሕዝብ ግልጽ የሚደረግ ወይም ሊደረግ የሚችል መሆኑን አስቀድሞ የሚያውቅ ከሆነ፤

ሐ) መረጃው አስቀድሞ ለሕዝብ ግልጽ ተደርጎ ከሆነ፤

መ) መረጃው የግለሰብን የአእምሮ ወይም የአካል ደኅንነት የሚመለከት ከሆነና ግለሰቡ በመረጃ ጠያቂ ሞግዚትነት ስር የሚተዳደር ሆኖ፦

(1) ፲፰ አመት ያልሞላው ከሆነ፤ ወይም

(2) የጥያቄውን ጸባይ ለመረዳት የማይችል ከሆነና መረጃውን መስጠቱ ለሦስተኛ ወገን ጥቅም አስፈላጊ ከሆነ፡፡

ሠ) መረጃው በህይወት የሌለ ሦስተኛ ወገንን የሚመለከት ከሆነና፦

(1) የሟቹ የቅርብ ሥጋ ዘመድ በሆነ ሰው መረጃው እንዲገለጸ ከተጠየቀ፤

(2) የሟቹን የቅርብ ሥጋ ዘመድ የጽሁፍ ፍቃድ በያዘ ሰው መረጃው እንዲገለጽ ጥያቄ ከቀረበ፤ ወይም

(3) የሟች ውርስ አጣሪ፣ ንብረት አስተዳዳሪ፣ ኑዛዜ አስፈጻሚ ወይም ወራሽ በሆነ ሰው የመረጃ ጥያቄ ከቀረበ፡፡

b) If the third party was already aware that the information is, or could be, made public by the public body or private organization;

c) If the information is already in the public domain;

d) If the information concerns the mental or physical well-being of an individual who is under the guardianship of the requester, and the individual:

i. Is under 18 years of age; or

ii. Is unable to understand the nature of the request, and the disclosure of the information is in the best interest of the third party.

e) If the information concerns a deceased third party and:

i. The disclosure is requested by a next of kin of the deceased;

ii. The disclosure is requested by a person who has the written consent of a next of kin of the deceased; or

iii. The request is made by an administrator of the deceased's estate, an executor of the will, or a legal heir; or

ረ) በመንግሥት አካል ወይም በግል ድርጅት የሚሰራን ወይም ይሰራ የነበረን ግለሰብ የስራ ኃላፊነትና ደረጃ ጨምሮ ማዕረጉን፣ የስራ አድራሻውን፣ የስራ መደቡን፣ ደመወዙን እና ሌሎች ክፍያዎችን ወይም በስራ ላይ ያከናወናቸውን ተግባሮች ወይም ግለሰቡ ራሱ በሞላው መዝገብ ላይ ያሰፈረውን ስሙን የሚመለከት ከሆነ ነው፡፡

f) If the information concerns an individual who is or was an official or employee of a public body or private organization, and the information relates to their title, work address, position, rank, salary and other benefits, or the duties performed in the course of their employment, or the name of the individual as it appears on records they personally completed.

፫/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም የቅርብ ሥጋ ዘመድ ማለት የሚች ወላጅ፣ ተወላጅ፣ እህት ወይም ወንድም ሲሆን የትዳር አጋርን ያካትታል፡፡

3/ For the purposes of this Article, Next of Kin means a parent, descendant, sister, or brother of the deceased, and includes a spouse.

፲፪. <u>የሦስተኛ ወገን የንግድ መረጃ</u>

12. <u>Commercial Information of a Third Party</u>

፩/ የተጠየቀው መረጃ፡

1/ A request for information may be refused if the requested information:

ሀ) የሦስተኛ ወገንን የንግድ ሚስጢር የያዘ ከሆነ፤

a) Contains trade secrets of a third party;

ለ) የንግድ ሚስጢር ባይሆንም የሦስተኛ ወገንን የፋይናንስ፣ የንግድ፣ ሳይንሳዊ ወይም ቴክኒካዊ መረጃን የሚመለከት ከሆነ እና የመረጃው መገለጽ በሦስተኛ ወገን የንግድ ጥቅም ላይ ከፍተኛ ጉዳት የማስከተል ውጤት የሚኖረው ከሆነ፤ ወይም

b) Even if it is not a trade secret, concerns financial, commercial, scientific, or technical information of a third party and its disclosure would likely cause significant harm to the commercial interests of that third party; or

ሐ) ለሌላ እንደማይገለጽበት በማመን በእምነት የተሰጠ የንግድ መረጃን የያዘ እና የመረጃው መገለጽ በውል ወይም በሌላ ድርድር ላይ ሦስተኛ ወገንን ተገቢ ላልሆነ ጉዳት ሊያጋልጥ የሚችል ወይም የሦስተኛ ወገንን የንግድ ውድድር የሚጎዳ ከሆነ የመረጃ ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

c) Contains commercial information supplied in confidence with the expectation that it will not be disclosed, and its disclosure could expose the third party to undue harm in contract or other negotiations, or prejudice the commercial competition of the third party.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም በሚከተለው ሁኔታ መረጃው ሊገለጽ ይችላል፦

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the information may be disclosed if:

ሀ) መረጃው አስቀድሞ ለሕዝብ ግልጽ ተደርጎ ከሆነ፤

a) the information is already in the public domain;

ለ) ሦስተኛ ወገን መረጃው እንዲሰጥ በጽሁፍ ከፈቀደ፤

b) the third party has consented in writing to the disclosure of the information;

ሐ) የመንግሥት አካልን የገንዘብ ወጪ የያዘ ከሆነ፤

c) it concerns the financial expenditures of a public body;

መ) ሦስተኛ ወገን በሰጠው ወይም ባስተላለፈው ውሳኔ ተጠያቂነትንና ግልጽነትን የሚያበረታታ ከሆነ፣

d) its disclosure promotes accountability and transparency in a decision made or passed by the third party;

ሠ) ሕገ-ወጥ ድርጊትን ወይም ጥፋትን የሚያጋልጥ ከሆነ፤ ወይም

e) it exposes illegal acts or misconduct; or

ረ) በሦስተኛ ወገን ስም የተመረተን ማንኛውንም ነገር ወይም የከባቢ ደኅንነት አስመልክቶ የተከናወነ የሙከራ ወይም የምርምር ስራን የሚመለከት ከሆነ እና የመረጃው መገለጽ በሕዝብ ወይም በከባቢ ደኅንነት ላይ ሊደርስ የሚችል አደጋን ለማሳወቅ አስፈላጊ የሆነ እንደሆነ ነው፡፡

f) it concerns any product manufactured in the name of a third party, or the results of testing or research conducted regarding environmental safety, and the disclosure is necessary to inform the public about potential risks to public or environmental safety.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፪) ፊደል ተራ (ረ) ቢኖርም የሙከራ ወይም የምርምር ዘዴዎችን ለማዳበር የተደረጉ ቅድመ ሙከራዎችን ወይም ምርምሮችን መረጃ አያካትትም።

3/ Notwithstanding paragraph (f) of Sub-Article (2) of this Article, the disclosure requirement does not include information on preliminary tests or research conducted specifically to develop testing or research methods.

፲፫. በእምነት የተሰጠ የሦስተኛ ወገን መረጃ

13. Third-Party Information Provided in Confidence

፩/ የተጠየቀው መረጃ፡-

1/ A request for information shall be refused if the requested information:

ሀ) የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት መገለጽ የሌለበት የመረጃ ልውውጥን በሚመለከት ያደረገውን የውል ግዴታ እንዲያፈርስ በማድረግ በተዋዋዩ ወገን ክስ ሊያስመሰርትበት የሚችል ከሆነ፤ ወይም

a) would cause the public body or private organization to breach a contractual obligation regarding the non-disclosure of an exchange of information, thereby potentially making it liable to a lawsuit by the contracting party; or

ለ) ሦስተኛ ወገን እንደማይገለጽበት በማመን የሰጠውን መረጃ የሚመለከት ሆኖ የመረጃው መገለጽ ወደፊት ከተመሳሳይ ምንጭ የሚገኝ ተመሳሳይ መረጃ መቀበልን ሊያስተጓጉል የሚችል ከሆነ እና የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት ለሕዝብ ጥቅም ሲባል መረጃዎቹን በየጊዜው መቀበል ያለበት ከሆነ የመረጃ ጥያቄው ውድቅ መደረግ ይኖርበታል።

b) concerns information provided by a third party in the belief that it would not be disclosed, and where its disclosure is likely to impede the future supply of similar information from the same source, and the public body or private organization has a public interest in continuing to receive such information regularly.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) ቢኖርም ሦስተኛ ወገን መረጃው እንዲሰጥ በጽሁፍ ከፈቀደ ለመረጃ ጠያቂ መሰጠት ይኖርበታል።

2/ Notwithstanding the provisions of paragraph (a) of Sub-Article (1) of this Article, the information shall be provided to the requester if the third party gives written consent for its disclosure.

፲፬. ሦስተኛ ወገንን ማሳወቅና ጣልቃ ስለማስገባት

፩/ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት በዚህ አዋጅ መሰረት የቀረበለት የመረጃ ጥያቄ ሦስተኛ ወገንን የሚመለከት ከሆነ እና መረጃውን ለጠያቂ ለመስጠት ካሰበ ጥያቄው በደረሰው በ፯ ቀናት ውስጥ መረጃውን የጠየቀውን ሰው ስም፣ የጠየቀውን የመረጃ ይዘት እና መረጃው መገለጽ ይኖርበታል የሚልበትን ምክንያት በመዘርዘር ሦስተኛ ወገን ተቃውሞ ካለው ይህንኑ በ፯ ቀናት ውስጥ እንዲያቀርብ በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ጥያቄ የቀረበለት ሦስተኛ ወገን የመረጃው መገለጽን የተቃወመ እንደሆነ የመረጃ ኃላፊ የሦስተኛ ወገን መልስ በደረሰው በ፯ ቀናት ውስጥ በመረጃው መገለፅ ወይም አለመገለጽ ላይ ውሳኔ በመስጠት ለመረጃ ጠያቂና ለሦስተኛ ወገን ያሳውቃል፡፡

፫/ የመረጃ ኃላፊ የተጠየቀውን መረጃ ለመረጃ ጠያቂ ለመስጠት ከወሰነ መረጃውን ለመረጃ ጠያቂ ከማስተላለፉ በፊት የሦስተኛ ወገኝ ይግባኝ ማቅረቢያ ጊዜ ገደብ እስከሚያበቃ ወይም በቀረበው ይገባኝ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ መጠበቅ አለበት፡፡

14. Notification and Intervention of Third Parties

1/ Where a public body or a private organization receives an information request under this Proclamation that concerns a third party and intends to disclose that information to the requester, it shall, within 7 days of receiving the request, notify the third party in writing. The notice shall specify the name of the requester, the content of the requested information, and the reasons why the information should be disclosed, and shall state that the third party may submit an objection within 7 days.

2/ Where a third party notified pursuant to Sub-Article (1) of this Article objects to the disclosure of the information, the information officer shall, within 7 days of receiving the third party's response, make a decision on whether or not to disclose the information and notify both the requester and the third party.

3/ If the information officer decides to grant the information request, they must wait until the time limit for the third party to file an appeal has expired, or until a final decision is rendered on a filed appeal, before transferring the information to the requester.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ጥያቄ የሚቀርብለት ሦስተኛ ወገን አድራሻ ካልታወቀ ወይም ተቃውሞ ካላቀረበ ተቃውሞ እንደሌለው ተቆጥሮ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት ውሳኔ ይሰጥበታል።

4/ If the address of the third party to be notified under Sub-Article (1) of this Article is unknown, or if the third party fails to submit an objection, it shall be deemed that there is no objection, and a decision shall be made in accordance with Sub-Article (2) of this Article.

፲፭. <u>የግለሰብና የንብረት ደኅንነት መረጃ</u>

የተጠየቀው መረጃ መገለጽ፦

፩/ የግለሰብን ሕይወት ወይም አካላዊ ደኅንነት ለጉዳት ሊያጋልጥ ይችላል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ ካለ፤

፪/ የህንጻ ወይም የኮምፒውተርና የሌላ መገናኛ መሳሪያን ወይም የሕዝብ ማመላለሻ አገልግሎትን ጨምሮ ማንኛውንም አይነት የግለሰብን የንብረት መዋቅር ወይም የአሰራር ደኅንነት ሊያሰናክል ወይም ሊያደናቅፍ ይችላል የሚል ምክንያታዊ ጥርጣሬ ካለ፤ ወይም

፫/ በምስክሮች ጥበቃ መርሃ ግብር የሚሸፈን ግለሰብን ደኅንነት ለመጠበቅ የተበጁ ስልቶችን፣ እቅዶችንና አሰራሮችን ውጤታማነት ሊያደናቅፍ ወይም ሊያሰናክል የሚችል ከሆነ መረጃው መገለጽ የለበትም።

15. <u>Protection of Safety of Individuals and Property</u>

The disclosure the requested information shall be refused:

1/ If there is a reasonable suspicion that it could expose individual's life or physical safety to harm;

2/ If there is a reasonable suspicion that it could prejudice the security of a building, computer, or other communication device, or any type of individual property. including public transportation services structure or system or

3/ May prejudice or impair the effectiveness of strategies, plans, and procedures designed to protect the safety of an individual covered under a witness protection program.

፲፮. <u>የሕግ አስከባሪና የፍርድ ምርመራ ሥራ መረጃ</u>

፩/ የተፈጸመን ወይም ሊፈጸም የሚችል የሕግ ጥሰትን መመርመሪያ፣ መከታተያ፣ መግቻ ወይም መከላከያ ዘዴዎችን፣ ቴክኒኮችን፣ የአሰራር ሥነ-ሥርዓቶችን ወይም የተግባር መመሪያዎችን የሚመለከት መረጃ ከሆነ እና የመረጃው መገለጽ ለወንጀል አፈጻጸም ምቹ ሁኔታ በመፍጠር ውጤታማነታቸውን ሊያሰናክል ወይም ከሕግ ማምለጥን ሊያስከትል የሚችል ከሆነ መረጃው መገለጽ የለበትም።

፪/ የተጠየቀው መረጃ የሚመለከተው የወንጀል ተጠርጣሪ ክስ ገና በዝግጅት ላይ ያለ ከሆነ ወይም ዝግጅቱ ቢጠናቀቅም ክሱ ገና ያልተጀመረ ከሆነ ወይም ክሱ በመታየት ላይ ያለ ከሆነና የመረጃው መገለጽ ወይም መረጃው መኖሩን ወይም አለመኖሩን ማረጋገጥ፦

ሀ) ክሱን ሊያሰናክል የሚችል፤

ለ) የፍትሕ ማስተጓጎል ሊያስከትል የሚችል፤ ወይም

ሐ) የፍርድ ሂደትን ሚዛናዊነት ወይም ገለልተኝነት ሊያዛባ የሚችል ከሆነ መረጃው መገለጽ አይኖርበትም።

16. <u>Law Enforcement and Legal Investigation Information</u>

1/ Information shall not be disclosed if it relates to methods, techniques, procedural rules, or operational guidelines for investigating, monitoring, curbing, or preventing a violation of the law that has been committed or may be committed, and where the disclosure of such information would hinder their effectiveness by creating favorable conditions for the commission of a crime or by facilitating evasion of the law.

2/ Information shall not be disclosed if it concerns a criminal suspect whose charges are still being prepared, or if the preparation is complete but the charge has not yet been filed, or if the case is currently pending before a court, and where the disclosure of the information or confirming its existence or non-existence:

a) Could prejudice the case;

b) Could result in the obstruction of justice; or

c) Could distort the balance or impartiality of the judicial process.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም የተጠየቀው መረጃ በቁጥጥር ስር ወይም በሕግ ጥበቃ ሥር ስላሉ ሰዎች አጠቃላይ የአያያዝ ሁኔታ የሚመለከቱ መረጃዎችን ብቻ የያዘ ከሆነ የመረጃ ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ አይገባም።

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a request for information shall not be refused if the requested information solely concerns the general conditions of treatment of persons who are in custody or under legal protection.

፲፯. <u>የሕግ ጥበቃ የሚደረግላቸው መረጃዎች</u>

17. <u>Legally Privileged Information</u>

፩/ የቀረበው ጥያቄ በክስ ክርክር ላይ ተከራካሪ የሆነው ወገን ለሦስተኛ ወገን እንዲገልጽ በሕግ የማይገደድበት መረጃ ለማግኘት የቀረበ ከሆነ የዚህ ልዩ መብት ተጠቃሚ የሆነው ሰው ካልፈቀደ በስተቀር መረጃው መገለጽ የለበትም።

1/ A request for information shall be refused if it seeks information that a party in legal proceedings is not legally compelled to disclose to a third party, unless the person who is the beneficiary of such privilege consents to the disclosure.

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም በሕግ ጥበቃ የተደረገለት መረጃ በሙያ የሥራ አጋጣሚ ታካሚ ከህክምና ባለሙያ፣ ደንበኛ ከሕግ አማካሪ ወይም ባለሙያ፣ መረጃ አፈትላኪ ወይም ሰጪ (የመረጃ ምንጭ) ከጋዜጠኛ፣ ባል ከሚስት ወይም ሚስት ከባል ጋር በነበራቸው ሕጋዊ ግንኙነት ወቅት የተገኘን ወይም የታወቀ መረጃ ያካትታል።

2/ For the purposes of Sub-Article (1) of this Article, privileged information includes information obtained or known during professional or legal relationships, such as those between a patient and a medical professional; a client and a legal advisor or professional; a whistleblower or informant and a journalist; or a husband and wife during their marriage.

፲፰. <u>የመከላከያና የሀገር ደኅንነት መረጃ</u>

18. <u>Defense and National Security Information</u>

፩/ እንዲሰጥ ወይም መኖር አለመኖሩ እንዲረጋገጥ የተጠየቀው መረጃ መገለጽ ወይም መረጋገጥ የሀገሪቱን መከላከያ ወይም የሀገርን ጸጥታና ደኅንነት ሊጎዳ የሚችል ከሆነ ጥያቄው ውድቅ መደረግ ይኖርበታል።

1/ A request for information shall be refused if the disclosure of the requested information, or the confirmation of its existence or non-existence, would prejudice the national defense or the security and safety of the country.

፪/ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የሀገር መከላከያ ወይም ጸጥታና ደህንነት መረጃ ማለት የጠላትን ወይም የአማጽያንን እንቅስቃሴዎች ለመከታተል እና ለመቆጣጠር ከሚደረግ ማንኛውም ዓይነት ተግባር ጋር የተያያዘ መረጃ ሆኖ፦

ሀ) ወታደራዊ ግዳጆችን፣ ልምምዶችን፣ ታክቲኮችን ወይም ስትራቴጂዎችን፤

ለ) የጦር መሳሪያዎችን ወይም ሌሎች አይነት መሳሪያዎችን ወይም ለጦር መሳሪያነት ወይም ለተመሳሳይ ተግባር እንዲያገለግሉ ታስበው የተነደፉ፣ የተበጁ፣ የዳበሩ ወይም የተመረቱ ማንኛቸውንም ነገሮች ብዛት፣ አይነት፣ አቅም፣ ጉልበት፣ደካማ ጎን፣ አሰራር፣ ብቃት፣ እንቅስቃሴ ወይም አጠቃቀም፤

ሐ) ኃላፊነት የተጣለበትን ሰው ባህሪ፣ ብቃት፣ ደካማ ጎን፣ ተግባር፣ እምቅ ችሎታ፣ ስምሪት ወይም እንቅስቃሴ፤

መ) መረጃ መሰብሰቢያ፣ መገምገሚያ ወይም መያዣ ዘዴዎችን ወይም ለዚሁ አገልግሎት የሚውሉ ሳይንሳዊ ወይም ቴክኒካዊ መሳሪያዎችን፤

ሠ) ሚስጢራዊ መረጃ አቀባዮችን እና ማንኛውንም ሌላ የመረጃ ምንጭን ማንነት፤ እና

ረ) በሀገሪቱ ወይም በሀገሪቱ ስም በዓለም አቀፋዊ ምክክሮችና ውይይቶች ላይ ጥቅም ላይ የሚውልን የጸጥታ መረጃ (ኢንተለጀንስን) የሚመለከቱ መረጃዎችን ያካትታል።

2/ For the purpose of this Proclamation, national defense or security and safety information means information related to any type of activity conducted to monitor and control the activities of enemies or insurgents, and includes information concerning:

a) military missions, exercises, tactics, or strategies;

b) the quantity, type, capability, power, weakness, operation, effectiveness, movement, or usage of weapons or any other types of equipment designed, customized, developed, or manufactured for military or similar purposes;

c) the character, capability, weakness, function, potential, deployment, or movement of a person assigned with responsibility;

d) methods of information collection, evaluation, or storage, or scientific or technical equipment used for such purposes;

e) the identity of confidential informants and any other source of information; and

f) intelligence used by the country, or in the name of the country, during international consultations and discussions.

፫/ ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም የጠላትና አማጽያን እንቅስቃሴ ማለት፦

ሀ) በሀገሪቱ ላይ የተቃጣ የወረራ ድርጊት፤

ለ) በሀገሪቱ ወይም በሕዝቡ ወይም በሀገሪቱ ስትራቴጂካዊ ጥቅሞች ላይ ያነጣጠረ የውስጥ ወይም የውጭ የአሻጥር ወይም የሽብር ተግባር፤

ሐ) ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት በሃይል ወይም በአመጽ ለመለወጥ የሚደረግ እንቅስቃሴ፤ ወይም

መ) ማንኛውም የውጭ ሀገር የስለላ ተግባር ወይም የጠላት እንቅስቃሴ ነው።

3/ For the purpose of this Proclamation, activities of enemies and insurgents means:

a) an act of invasion directed against the country;

b) an act of domestic or foreign sabotage or terrorism targeted at the country, its people, or its strategic interests;

c) an activity to change the constitutional order by force or violence; or

d) any foreign espionage activity or enemy movement.

፲፱. <u>የዓለም አቀፍ ግንኙነት መረጃ</u>

፩/ እንዲሰጥ ወይም እንዲረጋገጥ የተጠየቀው መረጃ መገለጽ ወይም መረጋገጥ የሀገሪቱን ዓለም አቀፋዊ ግንኙነት ሊጎዳ የሚችል ከሆነ የመረጃ ጥያቄው ውድቅ መደረግ አለበት።

19. <u>International Relations Information</u>

1/ A request for information shall be refused if the disclosure of the information, or the confirmation of its existence or non-existence, would prejudice the international relations of the country.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ በንዑስ አንቀጹ የተመለከተው መረጃ፦

ሀ) በዓለም አቀፍ ስምምነት ወይም ድርድር መሰረት ጉዳዩ በሚስጢር እንዲጠበቅለት ለሚፈልግ ዓለም አቀፍ ድርጅት ወይም ሌላ መንግሥት በሀገሪቱ ወይም በሀገሪቱ ስም የተሰጠ መረጃን፤

2/ Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the information referred to in the Sub-Article includes:

a) information given by the country, or in the name of the country, to an international organization or another government which requires the matter to be kept confidential in accordance with an international agreement or negotiation;

ለ) በዓለም አቀፍ ስምምነት ወይም በዓለም አቀፍ ልማዳዊ ሕግ መሰረት በሚስጢር መጠበቅ ያለበት መረጃን፤

ሐ) በሀገሪቱ ወይም በሌላ መንግሥት ወይም ዓለም አቀፋዊ ድርጅት እየተደረጉ ባሉ ወይም ወደፊት በሚደረጉ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ላይ በመንግሥት ወይም በሌላ የውጪ ሀገር መንግሥት ወይም ዓለም አቀፋዊ ድርጅት የተያዙ ወይም የሚያዙ አቋሞችን የሚመለከት መረጃን ወይም

መ) ከሌላ መንግሥት ወይም ዓለም አቀፍ ድርጅት ጋር የተደረጉ የሚስጥር ዲፕሎማሲያዊ የመልእክት ልውውጦችን ወይም ከሀገሪቱ ዲፕሎማቲክ ሚሲዮን ወይም ቆንስላ መስሪያ ቤቶች ጋር የተደረጉ ይፋዊ የመልእክት ልውውጦችን የሚመለከቱ መረጃዎችን ያካትታል።

b) information that must be kept confidential pursuant to an international agreement or international customary law;

c) information concerning positions taken, or to be taken, by the government or another foreign government or international organization in ongoing or future international negotiations; or

d) information relating to confidential diplomatic communications with another government or international organization, or official communications with the country's diplomatic missions or consular offices.

፳. <u>የኢኮኖሚ እና የፋይናንስ መረጃ</u>

፩/ እንዲሰጥ ወይም መኖር አለመኖሩ እንዲረጋገጥ የቀረበ የኢኮኖሚ ወይም የፋይናንስ መረጃ ጥያቄ በሚከተለው ሁኔታ ውድቅ ሊደረግ ይችላል፦

ሀ) የመረጃው መገለጽ በሀገሪቱ ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ላይ ጉዳት የሚያስከት ከሆነ፤

ለ) የፋይናንስ ደህንነት ጉዳት ላይ ሊጥል የሚችል ከሆነ፤ ወይም

ሐ) የመንግሥትን የሀገሪቱን ኢኮኖሚ የማስተዳደር አቅም የሚያዳክም ከሆነ ነው።

20. <u>Economic and Financial Information</u>

1/ A request for economic or financial information to be provided, or for confirmation of its existence or non-existence, may be refused under the following circumstances:

a) if the disclosure of the information would cause harm to the economic interests of the country;

b) if it could endanger financial security; or

c) if it weakens the government's capacity to manage the country's economy.

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንኡስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም የኢኮኖሚ ጥቅም ወይም የፋይናንስ ደህንነት መረጃ፡

ሀ) በስራ ላይ ባለ ገንዘብ፣ ቅንስናሽ ሳንቲሞች፣ ሕጋዊ ጨረታ፣ የውጪ ምንዛሬ ተመን ወይም የውጪ መዋዕለ ንዋይ ላይ ተዕእኖ ሊያስከትል የሚችል የፖሊሲ ለውጥ የማድረግ ወይም ያለማድረግ ውጥንን፤

ለ) በስራ ላይ ያለ የብድር ወይም የወለድ ተመንን፣ የጉምሩክ ወይም የኤክሳይስ ቀረጥን፣ የግብር ወይም ማናቸውም ሌላ የመንግሥት የገቢ ምንጮችን፣ የመንግሥት የፋይናንስ ተቋማት ቁጥጥርን ወይም ክትትልን፣ የመንግሥት ብድርን፣ የሸቀጦች ወይም የአገልግሎቶች ዋጋን፣ ኪራዮችን፣ የደመወዝ ወይም የቀን ክፍያዎችን ወይም ሌሎች ገቢዎችን የሚመለከቱ ቁጥሮችን የመለወጥ ወይም እንዳለ የማቆየት ውሳኔ ውጥንን፤

ሐ) የመንግሥት አካልን ንብረቶች ሽያጭን፣ ይዞታን የሚመለከቱ ውጥኖችን ወይም ዓለም አቀፍ የንግድ ስምምነቶችን፤ ወይም

መ) የመንግሥት አካልን የአክሲዮን ድርሻ ወይም ጥቅም የመንግሥት አካል ላልሆነ ለማንኛውም ሰው ለማስተላለፍ የተደረገን ስምምነት ወይም ውጥን ስምምነት ያካትታል።

2/ For the purpose of Sub-Article (1) of this Article, economic interest or financial security information includes:

a) plans to change or maintain policies that could affect the currency in circulation, coinage, legal tender, foreign exchange rates, or foreign investment;

b) planned decisions to change or maintain figures relating to current credit or interest rates, customs or excise duties, taxes or any other government revenue sources, the regulation or supervision of government financial institutions, public debt, the price of goods or services, rents, wages or daily rates, or other forms of income;

c) plans regarding the sale or holding of assets of a public body, or international trade agreements; or

d) an agreement or a planned agreement to transfer shares or interests of a public body to any person who is not a public body.

፳፩. <u>የመንግሥት ደርጅት የንግድ እንቅስቃሴ መረጃ</u>

፩/ እንዲሰጥ የተጠየቀው መረጃ፡

ሀ) የመንግሥት አካልን የአክሲዮን ድርሻ ወይም ጥቅም መንግሥታዊ አካል ላልሆነ ማንኛውም ሰው ለማስተላለፍ የተደረገ ስምምነት ወይም ውጥን ስምምነት፤

ለ) የመንግሥት ወይም የማንኛውንም የመንግሥት አካል የንግድ ሚስጢር፤

ሐ) ከንግድ ሚስጢር ባይካተትም መገለጹ የማንኛውንም መንግሥታዊ አካል ጥቅም የሚጎዳ የፋይናንስ፣ የንግድ፣ የቴክኒክ ወይም የሳይንስ መረጃ፤ ወይም

መ) ቢገለጽ ማንኛውም የመንግሥት አካል የሚያደርገውን የንግድ ውድድር ሊጎዳ የሚችል መረጃ የያዘ ከሆነ የመረጃ ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ ይችላል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተደነገገው ክልከላ ተግባራዊ የሚደረገው መረጃው አስቀድሞ ለሕዝብ ይፋ ካልተደረገ ወይም የመረጃው ባለቤት የሆነ የመንግሥት አካል መረጃው እንዲገለጽ በጽሑፍ ካልፈቀደ ነው፡፡

21. <u>Commercial Information of Government Bodies</u>

1/ A request for information may be refused if the requested information:

a) concerns an agreement or a draft agreement made to transfer the shares or interests of a government body to any person who is not a public body;

b) contains trade secrets of the government or any public body;

c) contains financial, commercial, technical, or scientific information which, although not a trade secret, would harm the interests of a government body if disclosed; or

d) contains information that, if disclosed, could prejudice the commercial competition of a government body.

2/ The prohibition stipulated under Sub-Article (1) of this Article shall apply only if the information has not been previously disclosed to the public or if the government body that owns the information has not consented in writing to its disclosure.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠየቀው መረጃ በመንግሥት አካል ስም የተደረገ የምርት፣ የክባቢ ሙከራ ውጤት ወይም ምርመራ የሚመለከት ሆኖ ቢገለጽ በሕዝብ ወይም በክባቢ ደኅንነት ላይ ሊደርስ የሚችል ከባድ አደጋን የሚያጋልጥ ከሆነ መከልከል የለበትም።

3/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (2) of this Article, disclosure shall not be refused if the requested information concerns product or environmental testing results or research conducted in the name of a public body, and where its disclosure is necessary to expose a serious risk to public or environmental safety.

፳፪. <u>የካቢኔ ሰነድ</u>

የካቢኔ መረጃ ለማግኘት የቀረበ የመረጃ ጥያቄ በሚከተለው ሁኔታ ውድቅ ሊደረግ ይችላል፦

22. <u>Cabinet Documents</u>

A request for access to Cabinet information may be refused under the following circumstances:

፩/ ለካቢኔ እንዲቀርብ የተዘጋጀ ወይም ለካቢኔ ውይይት የቀረበ መረጃ ከሆነ፤ ወይም

1/ If the information was prepared for submission to the Cabinet or was presented for Cabinet discussion; or

፪/ የካቢኔ አስተያየት፣ ምክክር፣ ግምገማ፣ ምክረ ሐሳብ ወይም ቃለ-ጉባኤ የያዘ መረጃ ሆኖ የመረጃው መገለጽ፦

2/ If the information contains Cabinet opinions, consultations, evaluations, recommendations, or minutes, where the disclosure of such information:

ሀ) ውጤታማ የመንግሥት ፖሊሲ ቀረጻን የሚያስተጓጉል፤

a) impedes effective government policy formulation;

ለ) የፖሊሲን ስኬት የሚያሰናክል ውጤት የሚያስከትል፤

b) results in hindering the success of a policy;

ሐ) በካቢኔ መካከል የሚደረግ የውይይት ወይም የምክክር ሂደት የሚገድብ፤ ወይም

c) restricts the process of discussion or consultation within the Cabinet; or

መ) የሀገርን ደህንነት የሚጎዳ ከሆነ ነው።

d) harms national security.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ መረጃው ታትሞ እንዲወጣ ወይም ለመረጃ ጠያቂ እንዲሰጥ ካቢኔው ሊወስን ይችላል።

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, the Cabinet may decide to publish the information or provide it to the information requester.

፬/ ለዚህ አንቀጽ አፈጻጸም "ካቢኔ" ማለት የሚኒስትሮች ምክር ቤት ኮሚቴ ወይም ንዑስ ኮሚቴ ሲሆን በክልል ሕገ መንግሥት መሠረት በየደረጃው የተቋቋመ እስከ ወረዳ ድረስ ያለን ካቢኔ ያካትታል።

4/ For the purposes of this Article, "Cabinet" means the Council of Ministers, its committees, or sub committees, and includes cabinets established at various levels dowen to the woreda level in accordance with Regional Constitutions.

፳፫. <u>የመንግሥት የሥራ ሰነድ</u>

23. <u>Operations of Government Bodies</u>

፩/ የመረጃው መገለጽ፡-

1/ A request for information may be refused if the disclosure of the information:

ሀ) በመንግሥት አካል ውስጥ ወይም በተለያዩ የመንግሥት አካላት መካከል የሚደረግ ግልፅ የሃሳብ ልውውጥን፣ ምክክርን፣ ሪፖርትን፣ የውሳኔ ሃሳብን ወይም ውይይትን ውጤት የሚያዘባ ከሆነ፤

a) would distort or prejudice the outcome of a free exchange of ideas, consultation, report,recommendation, or discussion conducted within a government body or between various government bodies;

ለ) በዝግጅት ወይም በውጥን ላይ ያለን ፖሊሲ ወይም ለሕዝብ አስተያየት ክፍት ያልሆነ ረቂቅ አዋጅ ያለጊዜው እንዲገለጽ በማድረግ የፖሊሲውን ወይም የረቂቅ ሕጉን ስኬት የሚያሰናክል ውጤትን የሚያስከትል ከሆነ፤ ወይም

b) would cause the premature disclosure of a policy under preparation or design, or a draft proclamation not yet open for public comment, thereby resulting in the frustration of the success of the policy or the draft law; or

ሐ) የቁጥጥር፣ የኦዲት፣ የምርመራ ወይም የፍተሻ ቴክኒኮችንና ሥነ-ሥርዓቶችን የመሳሰሉ የውስጥ አሰራሮችን እና መመሪያዎችን የያዘ ከሆነና የመንግሥት አካልን የመከራ፣ የምርመራ ወይም የኦዲት አሰራሮችንና ዘዴዎችን ውጤታማነት ሊያስተጓጉል ይችላል የሚል ምክንያታዊ ግምት ካለ የመረጃ ጥያቄ ውድቅ ሊደረግ ይችላል።

c) contains internal procedures and guidelines, such as techniques and procedures for supervision, audit, investigation, or inspection, and there is a reasonable expectation that it could impede the effectiveness of the testing, investigation, or auditing procedures and methods of the public body.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም መረጃው በፍርድ ምርመራ ሂደት ሊሰጡ የሚገባቸውን ማብራሪያዎች ወይም ምክንያቶች የያዘ ከሆነ መከልከል የለበትም።

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, disclosure shall not be refused if the information contains explanations or reasons that ought to be provided during a judicial investigation process.

፳፬. <u>የሙያ ፈተና እና ምልመላ ሂደት መረጃ</u>

24. <u>Professional Examinations and Recruitment Processes</u>

፩/ ከአካዳሚክ ወይም ከሙያ ፈተና፣ ምልመላ ወይም መረጣ ሂደት ጋር በተገናኘ የፈተና፣ የምልመላ ወይም የመረጣ ሂደቱ ከመጠናቀቁ በፊት የመረጃው መገለጽ የዚያን የፈተና ወይም የምልመላ ወይም የመረጣ ሂደት አደጋ ላይ የሚጥል ከሆነ የመረጃ ጥያቄው ውድቅ ሊደረግ ይችላል።

1/ A request for information related to an academic or professional examination, recruitment, or selection process may be refused if the disclosure of the information before the completion of such examination, recruitment, or selection process would compromise the integrity of that process.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው መረጃ የአካዳሚክ ወይም የሙያ ፈተና፣ ምልመላ ወይም መረጣ ሂደት ከተጠናቀቀ በኋላ ለመረጃ ጠያቂ መከልከል የለበትም።

2/ The information referred to in Sub-Article (1) of this Article shall not be withheld from an information requester after the academic or professional examination, recruitment, or selection process has been completed.

፳፭. <u>በጥቅል የቀረበ የመረጃ ጥያቄ</u>

25. <u>Overly Broad Request</u>

፩/ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት በሚከተለው ሁኔታ የመረጃ ጥያቄን ውድቅ ሊያደርግ ይችላል፦

1/ A public body or a private organization may refuse a request for information under the following circumstances:

ሀ) ጥያቄው በጥቅል የቀረበ ከሆነ እና በጥቅል የቀረበን የመረጃ ጥያቄ እንዲያስተካክል እገዛና ድጋፍ ቢደረግም አመልካች በጥቅሉ ያቀረበውን ጥያቄ ካላስተካከለ፤

a) if the request is framed in general terms and the applicant fails to refine the request despite being provided with assistance and support to do so;

ለ) ከመጠኑ ብዛት የተጠየቀን መረጃ የመገልበጡ ወይም የመሰብሰቡ ስራ የመንግሥት አካልን ወይም የግል ድርጅት መደበኛ የሰው ሃይልና የቁሳቁስ አጠቃቀም የሚያዛባ ወይም መደበኛ ስራ የሚያስተጓጉል ከሆነ፤

b) if, due to the large volume of information requested, the work of copying or collecting the information would disproportionately divert the human and material resources of the public body or private organization or disrupt its regular operations;

ሐ) መረጃው በአንድ በተወሰነ ጊዜ እንዲታተም የሚያዝ ሕግ ወይም ትእዛዝ ኖሮ የመረጃ ጥያቄው ከቀረበበት እለት ጀምሮ መረጃው በ፳፩ ቀናት ውስጥ ታትሞ የሚወጣ ከሆነ፤ ወይም

c) if there is a law or order requiring the information to be published at a specific time, and the information is due to be published within 21 days from the date the request was submitted; or

መ) ለጠቅላላው ሕዝብ እንዲደርስ ታትሞ በወጣ ሕትመት ውስጥ መረጃው የተካተተ ከሆነ።

d) if the information is already included in a publication that has been made available to the public.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ጥያቄው ውድቅ ከተደረገ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፪ የተመለከተው ማስታወቂያ ጥያቄው ውድቅ የተደረገው በእርግጥም በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ላይ በተገለጸው ምክንያት አግባብ ስለመሆኑ የማረጋገጫ ቃል ማካተት አለበት።

2/ Where a request is refused pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the notice referred to under Article 32 of this Proclamation shall include a statement affirming that the refusal is indeed appropriate based on the grounds specified under Sub-Article (1) of this Article.

፳፮. <u>ተነጥሎ ስለሚሰጥ መረጃ</u>

26. <u>Severance</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አግባብ የሚገለጹ እና የተከለከሉ መረጃዎችን አካቶ የያዘን ሰነድ ለማግኘት የመረጃ ጥያቄ ሲቀርብ መገለጽ ያለባቸውን የሰነዱን ክፍሎች ወይም ገጾች ብቻ ነጥሎ በማውጣት መገለጽ አለባቸው።

1/ Where a request is made for a record containing both exempt and non-exempt information from disclosure under this Proclamation, the parts or pages of the record that are not exempt from disclosure shall be severed and disclosed.

፪/ ከሰነዱ ውስጥ የተወሰኑ ክፍሎችን ወይም ገጾች ነጥሎ ያወጣ የመረጃ ኃላፊ ተነጥሎ የወጣውን የሰነዱን ክፍል ወይም ገጽ ብዛትና መጠን ለአመልካች በማሳወቅ ተነጥሎ የወጣውን መረጃ ለጠያቂ መስጠት አለበት፡፡

2/ An information officer who severs specific parts or pages from a record shall notify the applicant of the number and volume of the severed parts or pages and provide the extracted information to the requester.

፳፯. <u>የእገዳ መነሳት</u>

27. <u>Lifting Exemptions</u>

፩/ የዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፲፩ እስከ ፳፫ ያሉት ድንጋጌዎች ቢኖሩም መረጃው ከተፈጠረ ወይም ከተከሰተ ከ፳፭ አመት በኋላ የማይገለጽ መረጃ እንደሆነ አይቆጠርም፡፡

1/ Notwithstanding the provisions of Articles 11 up to 23 of this Proclamation, information shall no longer be considered exempt from disclosure after 25 years have elapsed from the date the information was created or occurred.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ጊዜ ካለፈ በኋላ ማንኛውም ሰው መረጃውን ለማግኘት ጥያቄ ሊያቀርብ ይችላል፡፡ የመረጃ ጥያቄ የደረሰው የመረጃ ኃላፊ በዚህ አዋጅ መሠረት መረጃውን ለመረጃ ጠያቂ ሊሰጥ ይችላል፡፡

2/ After the period specified in Sub-Article (1) of this Article has expired, any person may submit a request to access the information. The information officer who receives such a request may provide the information to the requester in accordance with this Proclamation.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ቢኖርም የመረጃው መግለጽ የግለሰብን ህይወት ወይም አካላዊ ደህንነት፣ የሕዝብን ወይም የሀገርን ደህንነት፣ የኢኮኖሚ ጥቅም ወይም ዓለም አቀፍ ግንኙነት ለአደጋ የሚያጋልጥ ከሆነ መረጃው ላይገለጽ ይችላል፡፡

3/ Notwithstanding Sub-Article (2) of this Article, the information may continue to be withheld from disclosure if its release would endanger the life or physical safety of an individual, public or national security, economic interests, or international relations.

፳፰. <u>ስለመረጃ ምደባ</u>

ለዚህ አዋጅ አፈጻጸም በሌላ ሕግ እንዳይገለጽ የተመደበ መረጃ፦

28. <u>Classified Information</u>

For the implementation of this Proclamation, information classified by another law shall have its secrecy expire as follows:

ሀ) እጅግ ብርቱ ሚስጥር ከሆነ ከ፳ ዓመት በኋላ፤

a) If it is Top Secret, after 20 years;

ለ) ብርቱ ሚስጥር ከሆነ ከ፲ ዓመት በኋላ፤ እና

b) If it is Secret, after 10 years; and

ሐ) ሚስጥር ከሆነ ከ፲፭ ዓመት በኋላ ሚስጥራዊነቱ ቀሪ ይሆናል።

c) If it is Confidential, after 5 years.

፳፱. <u>የሕዝብ ጥቅም ማመዘን</u>

29. <u>Public Interest Override</u>

፩/ የዚህ ክፍል ድንጋጌ ቢኖርም በመረጃው መገለጽ ጥበቃ በተደረገለት ጥቅም ላይ የሚደርሰው ጉዳት ሊገኝ ከሚችለው የሕዝብ ጥቅም የሚበልጥ ካልሆነ በስተቀር የመረጃ ጥያቄው ውድቅ አይደረግም።

1/ Notwithstanding the provisions of the exemptions section, a request for information shall not be refused unless the harm caused to the protected interest by the disclosure of the information outweighs the public interest to be gained from such disclosure.

፪/ የመረጃ ኃላፊ በዚህ ክፍል ድንጋጌ መሰረት የመረጃ ጥያቄን ውድቅ ከማድረጉ በፊት የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ሐይለ-ቃል ለቀረበው የመረጃ ጥያቄ ተፈጻሚ መሆን አለመሆኑን ማረጋገጥ ይኖርበታል።

2/ Before refusing a request for information based on the provisions of this Part, an Information Officer must verify whether the provision of Sub-Article (1) of this Article applies to the request.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት በቅን ልቦና መረጃ የገለጸ ወይም እንዲገለጽ የፈቀደ ማንኛውም ሰው መረጃ በመገለጹ ወይም እንዲገለጽ በመፍቀዱ ምክንያት ለወንጀል፣ ለፍትሐብሔር ወይም ለአስተዳደራዊ ቅጣት አይዳረግም።

3/ Any person who, in good faith, discloses information or authorizes its disclosure pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall not be subject to criminal, civil, or administrative liability as a result of such disclosure or authorization.

ክፍል አራት

የመረጃ ጥያቄ አቀራረብ እና ምላሽ አሰጣጥ ሥነ ሥርዓት

PART FOUR

PROCEDURES FOR INFORMATION REQUESTS AND RESPONSES

፴. የመረጃ ጥያቄ አቀራረብ

፩/ ማንኛውም ሰው ወይም መገናኛ ብዙኃን በራሱ ወይም ሕጋዊ ውክልና ባለው ሰው አማካኝነት የሚፈልገውን የመረጃ ዓይነት፣ የመረጃ ማግኛ ቋንቋ እና ቅርጽ ለይቶ በመግለጽ የመረጃ ጥያቄውን በጽሑፍ ወይም ሊነበብ በሚችል የኤሌክትሮኒክስ ዘዴ ለሚመለከተው የመረጃ ኃላፊ ወይም ተወካይ ማቅረብ ይችላል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም መረጃ ጠያቂ የሚፈልገው መረጃ በእጁ ይገኛል ለሚለው የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት የሥራ ክፍል በቀጥታ የመረጃ ጥያቄውን ከማቅረብ አይከለከልም።

፫/ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት መረጃ ጠያቂ በቀላሉ ሊረዳው የሚችል ግልጽ የመረጃ መጠየቂያ ፎርም አዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊያደርግ ይችላል። ዝርዝሩ ተቋሙ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

30. Application for Access

1/ Any person or mass media may, in person or through a legally authorized representative, submit a request for information in writing or through a readable electronic method to the relevant information officer or their representative, specifying the type of information as well as the language and format in which the information is to be provided.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, a requester is not prohibited from directly submitting an information request to the specific department of the public body or private organization believed to possess the information.

3/ A public body or private organization may prepare and implement a clear information request form that is easily understandable to the requester. Details shall be determined by Directives issued by the Institution.

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ቢኖርም ማንበብና መጻፍ የማይችል ወይም በተለያየ ምክንያት የመረጃ ጥያቄን በጽሁፍ ማቅረብ የማይችል አመልካች በቃል እንዲያቀርብ ይደረጋል፡፡ የመረጃ ኃላፊ በቃል የቀረበን ጥያቄ በመረጃ መጠየቂያ ፎርም ላይ በመመላት ግልባጩን ለመረጃ ጠያቂ በመስጠት ድጋፍ እና እገዛ የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, an applicant who is unable to read or write, or who cannot submit a written request for any other reason, shall be permitted to submit the request orally. The information officer shall reduce to writing, in a prescribed form the request made orally and furnish the applicant with a copy of the written request.

፭/ የመረጃ ጥያቄ ያቀረበ መረጃ ፈላጊ፦

ሀ) የመረጃ ጥያቄ ለማቅረብ የአገልግሎት ክፍያ አይጠየቅም፤

ለ) ማንነቱን የሚገልጽ መታወቂያ ማቅረቡ በቂ ነው፤

ሐ) የመረጃ ጥያቄ ማቅረቡን የሚያሳይ መተማመኛ ሰነድ ማግኘት አለበት፤

መ) አስቸኳይ የመረጃ ጥያቄ ካልሆነ በስተቀር መረጃ ጠያቂ መረጃውን የፈለገበትን ምክንያት እንዲያስረዳ አይገደድም፡፡

5/ An information seeker who submits a request:

a) shall not be charged a service fee for submitting the request;

b) shall only be required to present a valid identity card;

c) shall obtain a receipt proving that the information request has been submitted;

d) shall not be compelled to explain the reason for requesting the information, unless it is an urgent request.

፮/ መረጃ ጠያቂ የሚያቀርበው ምክንያት ወይም የመረጃ ኃላፊ ለመረጃ ጥያቄው ምክንያት ሊሆን ይችላል ብሎ የሚያምነው ነገር መረጃ የመጠየቅና የማግኘት ነጻነትን አይገድብም፡፡

6/ Neither the reason provided by the requester nor any reason the information officer assumes to be the basis for the request shall be used to restrict the the right to seek and obtain information.

፴፩. ምላሽ መስጠት

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት የመረጃ ጥያቄ የደረሰው የመረጃ ኃላፊ በሰዓቱ የስራ ቀናት ውስጥ የተጠየቀውን መረጃ በክፍያ ወይም ያለክፍያ ለአመልካች መስጠት አለበት።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት መረጃ ጠያቂ የጠየቀውን መረጃ በክፍያ እንዲወስድ ከተወሰነ የመረጃ ኃላፊው የክፍያውን መጠንና የአከፋፈሉን ሁኔታ ለመረጃ ጠያቂ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት። ማስታወቂያ በተላከበትና ክፍያ በተፈጸመበት ቀን መካከል ያለው ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው የሰዓት የሥራ ቀናት ውስጥ አይካተትም።

፫/ እንዲሰጥ የተጠየቀው መረጃ በማይገለጹ መረጃዎች ሥር የሚወድቅ ከሆነ በዚህ አዋጅ ክፍል ሦስት ክልከላን በተመለከተ የተቀመጡትን ምክንያቶች በመጥቀስ ጥያቄውን ያልተቀበለው እና ለበላይ ኃላፊ ቅሬታ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ ለመረጃ ጠያቂ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት።

31. Processing of Application

1/ An Information Officer who receives a request for information in accordance with this Proclamation shall provide the requested information to the applicant, with or without a fee, within 21 working days.

2/ Where it is decided that the requester shall obtain the information for a fee pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the Information Officer shall notify the requester in writing of the amount of the fee and the conditions of payment. The period between the sending of the notice and the payment of the fee shall not be included in the 21 working-day limit specified in Sub-Article (1).

3/ If the requested information falls under the category of exempt information, the Information Officer shall provide a written response to the requester stating that the request has been refused, citing the specific grounds for refusal provided under Part Three of this Proclamation, and informing the requester of their right to lodge a complaint with the Head.

፬/ እንዲሰጥ የተጠየቀው መረጃ በመንግሥት አካሉ ወይም በግል ድርጅት የማይገኝ ከሆነ ወይም በቂ ጥረት ተደርጎ ማግኘት ካልተቻለ የመረጃ ኃላፊ የተጠየቀውን መረጃ አለመያዙን ወይም ማግኘት አለመቻሉን እና ቅሬታ ማቅረብ እንደሚችል በመግለጽ ለመረጃ ጠያቂ በማረጋገጫ ቃል ጽሑፍ ማሳወቅ ይኖርበታል።

4/ If the requested information is not in the possession of the public body or private organization, or cannot be found despite diligent efforts, the Information Officer shall notify the requester in writing with a statement of confirmation, explaining that the information is not held or cannot be found, and informing them of the right to lodge a complaint.

፭/ ለመረጃ ጠያቂ የሚሰጥ ማንኛውም መረጃ በይዘትም ሆነ በቅርጽ እውነት እና ትክክለኛ ነው ተብሎ ይገመታል። መረጃ ጠያቂ የተሰጠውን መረጃ መሰረት አድርጎ ሊጠቀምበት ይችላል።

5/ Any information provided to a requester is presumed to be true and accurate in both content and form. The requester may utilize the provided information as a basis for their intended purpose.

፮/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተመለከተው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለመረጃ ጠያቂ ምንም አይነት ምላሽ አለመስጠት የተጠየቀን መረጃ ያለበቂ ምክንያት እንደመከልከል ይቆጠራል።

6/ A failure to provide any response to the requester within the time limit specified in Sub-Article (1) of this Article shall be deemed a refusal of the information request without sufficient cause.

፴፪. <u>የጊዜ ገደብ ስለማራዘም</u>

32. <u>Extension of Time Limits</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ ላይ የተደነገገው የመረጃ ጥያቄ ምላሽ መስጫ ቀን ቢኖርም የመረጃ ጥያቄ የደረሰው የመረጃ ኃላፊ በሚከተሉት ምክንያቶች ከ፲፬ ላልበለጡ ተከታታይ ቀናት ማራዘም ይችላል፦

1/ Notwithstanding the response time limit provided under Article 31 of this Proclamation, an Information Officer who receives a request for information may extend the period for no more than 14 consecutive days for the following reasons:

ሀ) በርካታ የመረጃ ጥያቄዎች የቀረቡ ከሆነ እና የተጠየቀውን መረጃ በ፳፩ የስራ ቀናት ውስጥ ለመስጠት የማይቻል ከሆነ፤

a) if a large number of information requests have been submitted and it is impossible to provide the requested information within 21 working days;

ለ) መረጃውን በተወሰነ ጊዜ ለመስጠት በርካታ ሰነዶችን ማገላበጥ የሚያስፈልግ በመሆኑ ምክንያት የመንግሥት አካልን ወይም የግል ድርጅት የሰው ኃይልና የቁሳቁስ አጠቃቀም የሚያዛባ ከሆነ፤

b) if the request requires searching through a large number of records to provide the information at a specific time, thereby disproportionately diverting the human and material resources of the public body or private organization;

ሐ) የተጠየቀውን መረጃ መፈለጉ፣ ማሰባሰቡ ወይም ማጠናቀሩ በተለያዩ ከተሞች ውስጥ ከሚገኙ ቅርንጫፍ መስሪያ ቤቶች የሚገኙ በርካታ መዛግብትን መመልከት የሚጠይቅ ከሆነ፤

c) if searching for, collecting, or compiling the requested information requires examining numerous records from branch offices located in different towns;

መ) የተፈለገውን መረጃ ለመስጠት ከልዩ ልዩ ክፍሎች ወይም ከሌሎች አካላት ጋር መመካከሩ ተገቢ ወይም አስፈላጊ ከሆነ እና በዚህም የተነሳ መረጃውን በ፳፩ የስራ ቀናት ውስጥ ለመስጠት የማይቻል ከሆነ፤ ወይም

d) if consultation with various departments or other bodies is appropriate or necessary to provide the requested information, and it is consequently impossible to provide the information within 21 working days; or

ሠ) መረጃ ጠያቂ ጊዜው ቢራዘም ፈቃደኛ መሆኑን በጽሁፍ የገለጸ እንደሆነ፡፡

e) if the requester has expressed in writing their consent to the extension of time.

፪/ የመረጃ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የጊዜ ገደቡ እንዲራዘም ከወሰነ የመረጃ ጥያቄ በደረሰው በ፳፩ ቀናት ውስጥ የመረጃ ጥያቄው ለተጨማሪ ቀናት የማራዘም ውሳኔ፣ ምክንያት እና ቅሬታ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ ለመረጃ ጠያቂ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

2/ If an Information Officer decides to extend the time limit pursuant to Sub-Article (1) of this Article, they shall, within 21 days of receiving the information request, notify the requester in writing of the decision to extend the request for additional days, the reason for the extension, and their right to lodge a complaint.

፫/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ ላይ የተደነገገው የጊዜ ገደብ ቢጠናቀቅም እንዲሰጥ የተጠየቀው መረጃ የሦስተኛ ወገን መረጃ ከሆነ የሦስተኛ ወገን ይግባኝ የመጠየቅ መብቱ ከመጠናቀቁ በፊት ወይም በሦስተኛ ወገን የቀረበ ይግባኝ እስካልተወሰነ ድረስ መረጃው ለመረጃ ጠያቂ ላይሰጥ ይችላል።

3/ Notwithstanding the expiry of the time limit provided under Article 31 of this Proclamation, if the requested information concerns a third party, the information may be withheld from the requester until the third party's right to appeal has expired or until an appeal filed by a third party has been decided.

፴፫. አስቸኳይ የመረጃ ጥያቄ

33. Urgent Information Requests

፩/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፩ ድንጋጌ ቢኖርም አስቸኳይ ለሆነ ጉዳይ የመረጃ ጥያቄ የደረሰው የመረጃ ኃላፊ በ፵፰ ሰዓታት ውስጥ ምላሽ መስጠት ይኖርበታል።

1/ Notwithstanding the provisions of Article 31 of this Proclamation, an Information Officer who receives an information request for an urgent matter shall provide a response within 48 hours.

፪/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አፈጻጸም አስቸኳይ የመረጃ ጥያቄ የሚባለው፦

2/ For the purposes of Sub-Article (1) of this Article, an urgent information request means:

ሀ) መረጃው በአስቸኳይ ካልተሰጠ በሰው ህይወት፣ ንብረት ወይም አካላዊ ደኅንነት ላይ በቅርብ ጊዜ ከባድ አደጋ ሊያስከትል ይችላል የሚያሰኝ ተጨባጭ ምክንያት መኖሩን የሚያሳይ ማመልከቻ የቀረበ እንደሆነ፤ ወይም

a) an application which demonstrates concrete reasons that failure to provide the information urgently could cause an imminent and serious danger to human life, property, or physical safety; or

ለ) በመገናኛ ብዙኃን ወይም መረጃ ለሕዝብ ማድረስ ወይም ማሰራጨት ዋነኛ ተግባሩ በሆነ መረጃ ጠያቂ በመንግሥት አካል ወይም በግል ድርጅት ተከናውኗል ወይም በቅርቡ ሊከናወን ነው የሚባልና ሕዝብ በአስቸኳይ ሊያውቀው ይገባል የሚያሰኝ ተጨባጭ ምክንያታዊ ጥያቄ የቀረበ እንደሆነ ነው።

b) a request submitted by the mass media or a requester whose primary function is the dissemination of information to the public, regarding an act performed or about to be performed by a public body or a private organization, which the public has an urgent and objective need to know.

፫/ የመረጃ ጥያቄው አስቸኳይ ለሆነ ጉዳይ መሆኑ ታምኖበት ለመረጃ ጠያቂ እንዲሰጥ ከተወሰነ መረጃው ያለክፍያ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት ለመረጃ ጠያቂ ይሰጣል፡፡

፬/ የቀረበው የመረጃ ጥያቄ አስቸኳይ አይደለም በሚል ውድቅ ከተደረገ የመረጃ ኃላፊ ጥያቄው በደረሰው በ፵፰ ሰዓታት ውስጥ ውሳኔውን እና ቅሬታ ወይም አስተዳደራዊ ይግባኝ የማቅረብ መብት ያለው መሆኑን በመግለጽ ለመረጃ ጠያቂ በጽሑፍ ምላሽ መስጠት አለበት፡፡

፴፬. <u>የመረጃ ጥያቄ ማስተላለፍ</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሰረት የመረጃ ጥያቄ የቀረበለት የሥራ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ እንዲሰጥ የተጠየቀው መረጃ በሥራ ክፍሉ የሚገኝ ሆኖ ጥያቄው ቀላል እና ግልጽ ከሆነ በራሱ ማስተናገድ ይኖርበታል፡፡ ሆኖም መረጃው በሥራ ክፍሉ ውስጥ የሌለ ከሆነ ጥያቄውን ለመረጃ ኃላፊ በማስተላለፍ በሕጉ መሰረት እንዲፈጸም ያደርጋል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የመረጃ ጥያቄው የተላለፈ እንደሆነ መረጃ ጠያቂ መልስ የሚያገኝበት የጊዜ ገደብ መቆጠር የሚጀምረው ጥያቄው ለሥራ ክፍሉ ከቀረበበት ጊዜ ጀምሮ ይሆናል፡፡

3/ If it is determined that the information request concerns an urgent matter and it is decided to grant the request, the information shall be provided to the requester free of charge within the timeframe specified in Sub-Article (1) of this Article.

4/ If a request is refused on the grounds that it is not urgent, the Information Officer shall, within 48 hours of receiving the request, provide a written response to the requester stating the decision and informing them of their right to lodge a complaint or an administrative appeal.

34. <u>Transfer of Information Request</u>

1/ In accordance with Article 30 Sub-Article (2) of this Proclamation, an official or employee who receives an information request shall handle the request themselves if the requested information is available within their department and the request is simple and clear. However, if the information is not available within the department, they shall transfer the request to the Information Officer to ensure it is processed in accordance with the law.

2/ If an information request is transferred pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the time limit for the requester to receive a response shall start counting from the date the request was initially submitted to the department.

፴፭. <u>መረጃ ማዘግየት</u>

፩/ የተጠየቀው መረጃ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ለማቅረብ የተዘጋጀ ሪፖርት ወይም የሪፖርቱ አካል ከሆነ የምክር ቤቱ ፭ ተከታታይ የመደበኛ ስብሰባ ቀናት እስኪያበቃ ድረስ የመረጃ ጥያቄን ማዘግየት ወይም ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ይቻላል።

፪/ የተጠየቀው መረጃ ተጠሪ ለሆነለት ወይም ለሌላ የመንግሥት አካል ለማቅረብ የተዘጋጀ ሪፖርት ወይም የሪፖርቱ አካል ከሆነ ሪፖርቱ ለሚመለከተው አካል እስኪቀርብ ድረስ ለመረጃ ጠያቂ መስጠትን ማዘግየት ወይም ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ ይቻላል። ሆኖም የመረጃ ጥያቄ ከቀረበበት ቀን አንስቶ ፴፭ ቀናት ካለፈው በኋላ መረጃ መስጠትን ማዘግየት ወይም ለሌላ ጊዜ ማስተላለፍ አይቻልም።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት የመረጃው መገለጽ ለሌላ ጊዜ እንዲተላለፍ ከተወሰነ ጥያቄው በደረሰ ከ፳፩ ባልበለጡ ቀናት ውስጥ የመረጃ ኃላፊ፡

ሀ) የመረጃ ማዘግየት ውሳኔ፤

ለ) ለውሳኔው መነሻ የሆነውን ሕጋዊ ምክንያት፤

ሐ) የተጠየቀው መረጃ የሚገለጽበት ጊዜ፤ እና

35. <u>Deferral of Information</u>

1/ If the requested information is a report, or part of a report, prepared for submission to the House of Peoples' Representatives, the information request may be deferred or postponed until the end of 5 consecutive regular session days of the House.

2/ If the requested information is a report, or part of a report, prepared for submission to a body to which the institution is accountable or to another public body, the disclosure may be deferred or postponed until the report is submitted to the relevant body. However, the disclosure of information may not be deferred or postponed for more than 35 days from the date the information request was submitted.

3/ Where a decision is made to defer the disclosure of information pursuant to Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the Information Officer shall, within no more than 21 days of receiving the request, notify the requester in writing of:

a) the decision to defer the information;

b) the legal grounds for the decision;

c) the time when the requested information will be disclosed; and

መ) መረጃ ጠያቂ ሪፖርቱ ለምክር ቤት ወይም ለሚመለከተው አካል ከመቅረቡ በፊት መረጃ እንዲሰጠው የፈለገበትን ምክንያት በቃል ወይም በጽሑፍ ለመረጃ ኃላፊ ማቅረብ እንደሚችል በመግለጽ ለመረጃ ጠያቂ በጽሑፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

d) that the requester may submit, orally or in writing, the reasons why the information should be provided before the report is submitted to the House or the relevant body.

፬/ የመረጃ ኃላፊ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (መ) የቀረበለትን አቤቱታ በመመርመር መረጃ መስጠትን ለተጠቀሰው የጊዜ ገደብ ማዘግየት በመረጃ ጠያቂ ላይ ጉዳት ሊያደርስ ይችላል የሚል በቂ ምክንያት ካለው ሪፖርቱ ለሚመለከተው አካል ከመቅረቡ በፊት የተጠየቀው መረጃ ለመረጃ ጠያቂ እንዲሰጥ ሊወሰን ይችላል፡፡

4/ The Information Officer shall examine the petition submitted under Paragraph (d) of Sub-Article (3) of this Article, and if there are sufficient grounds to believe that deferring the information for the specified period would cause harm to the requester, it may be decided to provide the requested information to the requester before the report is submitted to the relevant body.

፴፮. ክፍያ

36. Fees

፩/ መረጃ ጠያቂው

1/ An information requester shall not be charged any fee for:

ሀ) የጠየቀውን ሰነድ ለመፈለግ ወይም ለማሰባሰብ፤

a) searching for or collecting the requested document; or

ለ) የጠየቀው ሰነድ የማይገለጽ መረጃ አለመያዙን መርምሮ ለመወሰን ወይም የማይገለጽ መረጃን ከሰነድ ውስጥ ለመለረዝ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት ከሚያጠፋው ጊዜ ጋር በተያያዘ ምንም ዓይነት ክፍያ አይጠየቅም፡፡

b) the time spent by a public body or private organization examining the document to determine if it contains non-disclosable information or redacting non-disclosable information from the document.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ መረጃ ለማግኘት የሚከፈለው የገንዘብ ክፍያ በማንኛውም ሁኔታ መረጃውን የያዘውን ሰነድ ለማባዛት ከሚያስፈልገው ወጪ መብለጥ የለበትም፡፡

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (3) of this Article, the fee paid to obtain information shall in no circumstance exceed the actual cost required to reproduce the document containing the information.

፫/ በሚከተለው ሁኔታ በመረጃ ጠያቂ የማባዣ ወጪ ክፍያ አይፈጸምም፦

ሀ) የግል መረጃ፤

ለ) የመክፈል አቅም የሌለው ሰው፤

ሐ) በኤሌክትሮኒክ ዘዴ የሚባዛ መረጃ፤

መ) በመገናኛ ብዙሃን የሚጠየቅ የህዝብ የሕዝብ ጥቅም መረጃ፤ ወይም

ሠ) የመንግሥት አካል የማተም ግዴታ ያለበት ሆኖ ከ፳ ገጽ የማይበልጥ ሰነድ ለማግኘት የማባዣ ወጪ ክፍያ አይጠየቅም።

፬/ የግል ድርጅት የማባዣ ክፍያ ሳያስከፍል መረጃ መስጠት አይጠበቅበትም።

፭/ የዚህ አንቀጽ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በማማከር የመረጃ ክፍያ ተመን ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

3/ No reproduction fee shall be charged to a requester in the following circumstances:

a) for personal information;

b) for a person who lacks the capacity to pay;

c) for information reproduced through electronic methods;

d) information of public interest requested by the mass media; or

e) where a public body has a duty to publish the information and the document obtained does not exceed 20 pages.

4/ A private organization shall not be expected to provide information without charging reproduction fees.

5/ Without prejudice to the provisions of this Article, the institution shall issue a detailed Directive concerning information fees rates in consultation with the concerned bodies.

፴፯. <u>ሪፖርት የማቅረብ ግዴታ</u>

፩/ የመረጃ ኃላፊ ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ስላከናወናቸው ዝርዝር ተግባራት አመታዊ ሪፖርት ለተቋሙ የማቅረብ ግዴታ አለበት።

37. <u>Duty to Submit Report</u>

1/ An Information Officer shall have the duty to submit an annual report to the Institution regarding the detailed activities performed to implement this Proclamation.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የመረጃ ኃላፊ በዚህ አዋጅ ታትመው እንዲወጡ የታዘዙ መረጃዎች አፈጻጸም እና ሕዝብ መረጃውን የሚያገኝበት ሁኔታ ዝርዝር መግለጫ ለተቋሙ ሪፖርት ማቅረብ አለበት።

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Information Officer shall submit a report to the Institution detailing the implementation of information mandated to be published and the conditions under which the public accesses such information.

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚዘጋጀው ሪፖርት፡-

ሀ) በአመልካች የቀረቡ የመረጃ ጥያቄዎች ብዛት እና መግለጫ፤

ለ) በከፊል እና ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት ያገኙ የመረጃ ጥያቄዎች ብዛት እና መግለጫ፤

ሐ) በከፊል ወይም ሙሉ በሙሉ ውድቅ የተደረጉ የመረጃ ጥያቄዎች ብዛት እና መግለጫ፤

መ) ለበላይ ኃላፊ የቀረቡ ቅሬታዎች፣ በበላይ አካሉ የተሰጡ መፍትሔዎች እና ተቀባይነት ያገኙ ቅሬታዎች ብዛት እና መግለጫ መያዝ አለበት። ተቋሙ ዝርዝር የአፈጻጸም መመሪያ ያወጣል።

3/ The report prepared pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall include:

a) the number and description of information requests submitted by applicants;

b) the number and description of information requests granted in part or in full;

c) the number and description of information requests rejected in part or in full;

d) complaints submitted to the head of the body, the solutions provided by the head, and the number and description of complaints that were accepted. The Institution shall issue detailed implementation directives.

፬/ ማንኛውም የፌደራል መንግሥት አካል ከሆነ ለሚኒስትሮች ምክር ቤት እና ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት፤ የክልል መንግሥት አካል ከሆነ ደግሞ ለክልሉ ምክር ቤት እና ለክልሉ አስተዳደር ምክር ቤት አመታዊ የስራ አፈጻጸም ሪፖርቱን በሚያቀርብበት ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተውን የመረጃ ነጻነት ሪፖርት አካቶ ማቅረብ ይኖርበታል።

4/ Any federal public body shall include the freedom of information report referred to in Sub-Article (1) of this Article when submitting its annual performance report to the Council of Ministers and the House of Peoples' Representatives; likewise, a regional public body shall include it when reporting to the Regional Council and the Regional Administration Council.

፴፰. ቋንቋ እና ቅርጽ

፩/ አመልካች የጠየቀው መረጃ በመረጠው ቋንቋ የተዘጋጀ ከሆነ አመልካች በመረጠው ቋንቋ ይሰጠዋል።

፪/ መረጃው አመልካች በመረጠው ቋንቋ ያልተዘጋጀ ከሆነ መረጃው በተዘጋጀበት ቋንቋ ለአመልካች መሰጠት አለበት።

፫/ የመንግሥት አካልን ወይም የግል ድርጅትን የሰውና የቁሳቁስ ኃይል ያለአግባብ እንዲባክን ወይም መደበኛ ተግባር የሚያስት ወይም ለሰነዱ ደኅንነት አስጊ ካልሆነ በስተቀር መረጃ መሰጠት ያለበት መረጃ ጠያቂ ይሰጠኝ ባለበት አይነት ቅርጽና መንገድ ነው።

38. Language and Format

1/ If the requested information is available in the language chosen by the applicant, it shall be provided in that language.

2/ If the information is not available in the language chosen by the applicant, it shall be provided in the language in which it was originally prepared.

3/ Unless it causes an undue waste of human and material resources, disrupts regular functions, or endangers the security of the document, information shall be provided in the format and manner requested by the information seeker.

ክፍል አምስት

የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም

PART FIVE

THE ETHIOPIAN INSTITUTION OF THE OMBUDSMAN

፴፱. የመረጃ ነጻነት ዘርፍ ዕንባ ጠባቂ መቋቋም

፩/ የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም በማቋቋሚያ አዋጁና በሌሎች ሕጎች ከተሰጠው ሥልጣንና ተግባር በተጨማሪ ይህን አዋጅ የማስተግበር፣ አፈጻጸም የመቆጣጠርና የመከታተል እንዲሁም የአሰራር ግልጽነትና ተጠያቂነት እሴቶች እና የመረጃ ተደራሽነት ባህል መጎልበትና መዳበር አስፈላጊ የሆኑ ሌሎች ተግባራት የማከናወን ሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

39. Establishment of the Access to Information Ombudsman

1/ In addition to the powers and duties granted to it under its establishment proclamation and other laws, the Ethiopian Institution of the Ombudsman is hereby empowered by this Proclamation to implement, monitor, and follow up on the execution of this Proclamation, and to perform other activities necessary for the growth and development of values of transparency and accountability, and a culture of information accessibility.

፪/ በዚህ አዋጅ ለተሰጠው ተግባርና ኃላፊነት ውጤታማ አፈጻጸም በተቋሙ የመረጃ ነጻነት ዘርፍ ዕንባ ጠባቂ በምክር ቤት ይሾማል።

2/ For the effective execution of the duties and responsibilities granted under this Proclamation, an Information Freedom Sector Ombudsman shall be appointed by the House.

፫/ የመረጃ ነጻነት ዘርፍ ዕንባ ጠባቂ ተጠሪነቱ ለዋና ዕንባ ጠባቂ ሆኖ ከዋና ዕንባ ጠባቂ ጋር በመመካከር የሥራ ዘርፉን የመምራትና የማደራጀት፤ ሠራተኞች የመከታተልና የመመምራት፤ ወቅታዊና አመታዊ የክዋኔ ሪፖርት የማቅረብ እና በዋና ዕንባ ጠባቂ የሚሰጠውን ሌላ ተግባር የማከናወን ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል።

3/ The Information Freedom Sector Ombudsman shall be accountable to the Chief Ombudsman and, in consultation with the Chief Ombudsman, shall have the power and duty to lead and organize the sector, monitor and direct employees, submit periodic and annual performance reports, and perform other tasks assigned by the Chief Ombudsman.

፬/ በሌላ ሕግ በግልጽ ካልተደነገገ በስተቀር የመረጃ ነጻነት ሕግ ዘርፍ ዕንባ ጠባቂ ምልመላና መረጣ፣ ሹመት አሰጣጥ፣ የአገልግሎት ዘመን፣ ደመወዝ፣ ጥቅማጥቅም የመሳሰሉት በተቋሙ ማቋቋሚያ ሕግ አግባብ ይሆናል።

4/ Unless otherwise explicitly provided by another law, such as the recruitment, selection, appointment, term of service, salary, benefits, of the Information Freedom Sector Ombudsman shall be in accordance with the establishment law of the Institution.

፵. <u>ገለልተኛነት</u>

ተቋሙ የተሰጠውን ኃላፊነትና ተግባር ከማንኛውም አካል ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና ሌሎች ፍላጎቶችና ተጽዕኖዎች ነጻና ገለልተኛ በመሆን ማከናወን ይኖርበታል።

40. <u>Independence</u>

The Institution shall perform the responsibilities and duties assigned to it independently and neutrally, free from the political, economic, or any other interests and influences of any party.

፵፩. <u>በጀት</u>

፩/ ተቋሙ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ሥልጣንና ተግባር በተሟላ መልኩ ለማከናወን የሚያስፈልገው ተጨማሪ በጀት በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይመደብለታል።

41. <u>Budget</u>

1/ The additional budget required for the Institution to fully carry out the powers and duties granted to it under this Proclamation shall be allocated by the House of Peoples' Representatives.

፪/ ዓላማውንና ገለልተኛነቱን የማይጻረር ከተለያዩ አካላትና ተቋማት የገንዘብ እና ሌላ ድጋፍ ሊቀበልና ሊያገኝ ይችላል፡፡

2/ The Institution may receive and obtain financial and other support from various bodies and organizations, provided it does not contradict its objectives and independence.

፵፪. <u>የተቋሙ ሥልጣንና ተግባር</u>

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፱ ጠቅላላ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ የሚከተለው ሥልጣንና ተግባር ይኖረዋል፦

42. <u>Powers and Duties of the Institution</u>

Without prejudice to the general provisions of Article 39 of this Proclamation, the Institution shall have the following powers and duties:

፩/ የመረጃ ነጻነት ሕጎችን ያመነጫል፤ ያስፈጽማል፤

1/ To initiate freedom of information laws and ensure their enforcement;

፪/ የዚህን አዋጅና ድንጋጌዎች ዓላማ፣ አፈጻጸም እና አጠቃቀም ግልጽ ለማድረግ የሚረዱ ማብራሪያዎች እና መድብሎች ያዘጋጃል፤ አትሞ ያወጣል፤ ያሰራጫል፤

2/ To prepare, publish, and disseminate explanations and compendiums that help clarify the objectives, implementation, and application of this Proclamation and its provisions;

፫/ የመረጃ ነጻነት ሕግ አፈጻጸም ይቆጣጠራል፤ ይከታተላል፤ ያስፈጽማል፤ያስተዋውቃል፤

3/ To monitor, follow up on, enforce, and promote the implementation of freedom of information laws;

፬/ በዚህ አዋጅ የተሰጠውን ኃላፊነት ለመወጣት የሚያስፈልገውን አሰራር፣ ሂደት እና ተግባር ይወስናል፤ ተፈጻሚ ያደርጋል፤

4/ To determine and implement the procedures, processes, and activities necessary to fulfill the responsibilities granted under this Proclamation;

፭/ ከማንኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን የቀረበለትን አቤቱታ ወይም አስተዳደራዊ ይግባኝ መሰረት በማድረግ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተዘረዘሩትን ድንጋጌዎች የሚጥሱ ማናቸውንም ጥሰቶች ይመረምራል፤

5/ To investigate any violations of the provisions stipulated in this Proclamation based on complaints or administrative appeals submitted by any individual or group;

፮/ መረጃ ነጻነትን የተመለከተ ቅሬታ፣ ጥቆማ ወይም ጥያቄ ለመፍታት የምርመራ አስፈላጊነት፣ ዓይነት እና አካሄድ ይወስናል፤

6/ To determine the necessity, type, and manner of investigation required to resolve complaints, tips, or inquiries regarding freedom of information;

፯/ በዚህ አዋጅ መሰረት የሚቀርብለትን ጉዳይ ጥብቅ ባልሆነ የአሰራር ሥነ-ሥርዓት በፍጥነት ያከናውናል፤

፰/ ከመረጃ ነጻነት ጋር የተያያዘን ጉዳይ በድርድር፣ በስምምነት ወይም በግልግል ይፈታል፤

፱/ ምክረ ሐሳብ ይሰጣል፣ አስተዳደራዊ እርምጃ ይወስናል ወይም ፍትሐዊና ምክንያታዊ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ይሰጣል፤

፲/ መረጃው የማይገለጽ መሆን አለመሆኑን ለመወሰን ለመረጃ ጠያቂ የተከለከለን መረጃ ወይም ሰነድ አስቀርቦ ይመለከታል ወይም ይመረምራል፤

፲፩/ እንዲሰጥ የተጠየቀን መረጃ እንዳይገለጽ ያግዳል፤

፲፪/ በጥቅል የቀረበ ወይም በመስፈርቱ መሰረት ያልቀረበ የመረጃ ጥያቄ ውድቅ ያደርጋል፤

፲፫/ ግኝት፣ ምክረ ሐሳብ፣ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በየጊዜው አትሞ ያወጣል፣ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፤

፲፬/ መረጃ ነጻነትን በሚመለከት ዓለም አቀፍና አህጉራዊ ስብሰባ ወይም ውይይት ላይ ይሣተፋል፣ ሪፖርት ያቀርባል፣ ስምምነት ይፈራረማል።

፵፫. <u>ኦዲት እና ቁጥጥር ማድረግ</u>

፩/ ተቋሙ ይህ አዋጅ በመንግሥት አካል ስለመከበሩ ኦዲት ያደርጋል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተቋሙ ኦዲት የማድረግ ሥልጣን፦

ሀ) ፍተሻ ወይም ዳሰሳ ማካሄድ፤

7/ To process cases submitted to it under this Proclamation promptly and through flexible procedural rules;

8/ To resolve matters related to freedom of information through negotiation, conciliation, or mediation;

9/ To provide recommendations, take administrative measures, or issue fair and reasonable decisions or orders;

10/ To summon and inspect information or documents withheld from a requester in order to determine whether they are non-disclosable;

11/ To block the disclosure of requested information where appropriate;

12/ To reject information requests that are broadly framed or do not meet the requirements set forth;

13/ To periodically publish and make its findings, recommendations, decisions, or orders available to the public;

14/ To participate in international and regional meetings or discussions concerning freedom of information, submit reports, and sign agreements.

43. <u>Auditing and Supervision</u>

1/ The Institution shall audit the compliance of public bodies with this Proclamation.

2/ Pursuant to Sub-Article (1) of this Article, the auditing power of the Institution shall include:

a) Conducting inspections or surveys;

ለ) ለኦዲት ሥራው አስፈላጊ የሆነ ምርመራ ማድረግ፤

ሐ) የኦዲት ተደራጊን የመንግሥት አካል ሰራተኛ ማሳተፍ፤

መ) ለኦዲት ሥራው መረጃ እንዲቀርብ መጠየቅና ማግኘት፤

ሠ) ተጨማሪ መረጃ እንዲቀርብ ትእዛዝ መስጠት፤

ረ) በኦዲት የተለየ የተገዥነት ጥሰት እንዲታረም ትዕዛዝ ወይም የውሳኔ ሐሳብ መስጠት እና ስለአፈጻጸሙ ክትትል ማድረግ፤

ሰ) እንደአስፈላጊነቱ አዋጁን የማይፈጽም የመንግሥት አካል ለምክር ቤት ልዩ ሪፖርት ማቅረብ፤

ሸ) የተገዥነት ጥሰት ምክንያቶችን መመርመር ያካትታል።

b) Carrying out investigations necessary for the audit work;

c) Involving the employees of the public body being audited;

d) Requesting and obtaining information necessary for the audit work;

e) Ordering the submission of additional information;

f) Issuing orders or recommendations to correct identified compliance violations and monitoring their implementation;

g) Submitting a special report to the House, as necessary, regarding a public body that fails to implement the Proclamation;

h) Investigating the reasons for compliance violations.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ተቋሙ የዚህን አዋጅ ድንጋጌዎች አፈጻጸም አስመልክቶ በማንኛውም ጊዜ በመንግሥት አካል ወይም በግል ድርጅት ቁጥጥር ያደርጋል።

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Articles (1) and (2) of this Article, the Institution may, at any time, supervise the implementation of the provisions of this Proclamation by a public body or a private organization.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት የተቋሙ ቁጥጥር የማድረግ ኃላፊነት የሚከተሉትን ያካትታል፦

ሀ) ቁጥጥር ከመጀመሩ በፊት አስቀድሞ ለመንግሥት አካል ወይም ለግል ድርጅት በጽሑፍ ማሳወቅ፤

ለ) በቁጥጥር ወቅት ለተለየና ለተረጋገጠ ክፍተት በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲታረም ምክረ ሐሳብ መስጠት፤

4/ Pursuant to Sub-Article (3) of this Article, the supervisory responsibility of the Institution shall include:

a) providing prior written notice to the public body or private organization before starting supervision;

b) providing recommendations for the rectification of identified and verified gaps within a specified timeframe;

ሐ) የሰጠው ምክረ ሐሳብ ስለመፈጸሙ በተለያየ መንገድ ክትትል ማድረግ፤ ዝርዝር አፈጻጸሙ ተቋሙ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል፡፡

c) monitoring the implementation of its recommendations through various means. Detailed execution shall be determined by a Directive issued by the Institution.

፵፬. ጥናት እና ምክረ ሐሳብ

44. Study and Recommendation

፩/ ተቋሙ ለዚህ አዋጅ ዓላማ መሣካት አስፈላጊ ጥናት ያደርጋል፤ እንዲካሄድ ያደርጋል፡፡

1/ The Institution shall conduct or cause to be conducted necessary studies for the successful realization of the objectives of this Proclamation.

፪/ ለምክር ቤት በሚያቀርበው አመታዊ ሪፖርት ውስጥ የጥናትና የማሻሻያ ውሳኔ ወይም ምክረ ሐሳብ ማካተት አለበት፡፡

2/ The Institution shall include the results of such studies and its decisions or recommendations for amendments in its annual report to the House.

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፦

3/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (2) of this Article, the Institution shall:

ሀ) የዚህን አዋጅ ድንጋጌ ለማሻሻል፣ ለማጠናከር ወይም ለማዳበር የሚረዳ ምክረ ሐሳብ ለምክር ቤት ያቀርባል፤

a) submit recommendations to the House to amend, strengthen, or develop the provisions of this Proclamation;

ለ) አሰራሮችን ለማዳበርና ለማሻሻል የሚረዱ አጠቃላይ እና ወይም ዝርዝር የውሳኔ ሐሳቦችን ጉዳዩ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት ያቀርባል፡፡

b) provide general and or detailed recommendations to the relevant public body or private organization to develop and improve their procedures.

፵፭. ግንዛቤና ሥልጠና

45. Awareness and Training

፩/ ተቋሙ በመረጃ ነጻነት ዙሪያ ቀጣይነት ያለው የሥልጠናና የግንዛቤ ማስጨበጫ መርሐ ግብር በመቅረጽ ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

1/ The Institution shall design and implement a continuous training and awareness-raising program regarding freedom of information.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፦

2/ Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the Institution shall:

ሀ) መንግሥታዊ እና መንግሥታዊ ካልሆኑ ሌሎች አካላት ጋር በመተባበር በመረጃ ነጻነት ዙሪያ የሕዝብን ግንዛቤ የሚያዳብሩ ተግባራትን ያከናውናል፤ በዚህ አዋጅ የሚጠየቅ መስፈርትና ማንኛውም ሰው ያለውን መብት በተለያዩ ዘዴዎች ለሕዝብ ያሳውቃል፤

a) cooperate with governmental and non-governmental bodies to carry out activities that develop public awareness on freedom of information; and notify the public of the requirements of this Proclamation and the rights of every person through various methods;

ለ) ለመንግስት አካልና ለግል ድርጅት የመረጃ ኃላፊ እና ባለሙያ የሚሰጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ያዘጋጃል፤ ስልጠና ይሰጣል፤ያግዛል፤

b) prepare and provide awareness training and support for information officers and experts of public bodies and private organizations;

ሐ) የቴክኒክ ድጋፍ ማድረግን ጨምሮ በፈቃደኝነት ላይ የተመሰረተ የአቅም ግንባታ ሥራ ያከናውናል፤ በዚህ ሥራ ላይ ከተሰማራ የሲቪል ማኅበረሰብ፣ የትምህርት፣ የጥናትና ምርምር እና የሥልጠና ተቋም ጋር በትብብር ይሰራል፤

c) conduct voluntary capacity-building work, including technical support; and work in collaboration with civil society, educational, research, and training institutions engaged in such work;

መ) የመረጃ ነጻነት መድብልና ማብራሪያ ያዘጋጃል፤ ያሰራጫል፤

d) prepare and distribute freedom of information manuals and explanations;

ሠ) ለመንግስት ሰራተኞች የሚሰጥ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ይከታተላል፤ሥልጠና እንዲሰጥ ምክረ ሐሳብ ያቀርባል፤ ጥያቄ ሲቀርብ ስልጠና ይሰጣል፤

e) Monitor the awareness training provided to government employees; provide recommendations for training to be given; and provide training upon request;

ረ) ስለመረጃ ነጻነት አፈጻጸም በተለያየ መንገድ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

f) publicize the performance of freedom of information implementation through various means.

፫/ ከመረጃ ኃላፊ ወይም ከሌላ ሰው የሚቀርብን ጥያቄ ወይም ጥቆማ መሰረት በማድረግ ማብራሪያ ወይም ምክረ ሐሳብ ይሰጣል፡፡

3/ The Institution shall provide explanations or recommendations based on inquiries or tips received from an information officer or any other person.

፵፮. <u>የአፈጻጸም ሪፖርት</u>

፩/ ተቋሙ በዚህ አዋጅ መሰረት ከመረጃ ኃላፊ የተላከለትን የመረጃ ነጻነት ሕግ ትግበራ ሪፖርት ወይም በቁጥጥርና ክትትል የተለዩ ክፍተቶችን በማጠናቀርና በመተንተን አመታዊ ወይም ልዩ ሪፖርት ለምክር ቤት ያቀርባል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚቀርብ ልዩ ሪፖርት፦

ሀ) የመረጃ ነጻነት ድንጋጌንና በተቋሙ የተሰጠን ምክረ ሐሳብ ወይም ውሳኔ ለመፈጸም ፈቃደኛ ያልሆነ የመንግሥት አካል፣ የበላይ ኃላፊ እና የመረጃ ኃላፊ ሙሉ ሥምና አድራሻ፤

ለ) ሪፖርት ለማቅረብ መነሻ የሆነው ጉዳይ ወይም የመረጃ ነጻነት ድንጋጌ ጥሰት እና ለመንግሥታዊ አካሉ የቀረበ ምክረ-ሐሳብ ወይም ውሳኔ፤

ሐ) ለሪፖርቱ መነሻ በሆነው ጉዳይ ምክንያት በሕዝብ ወይም በግለሰብ መብትና ጥቅም ላይ የደረሰ ጉዳት ካለ፤

መ) ለመረጃ ነጻነት ድንጋጌ ጥሰት ወይም ለተቋሙ ምክረ-ሐሳብ የመንግሥታዊ አካሉ የጽሑፍ ወይም የቃል ምላሽና ምክንያት፤

46. <u>Performance Report</u>

1/ The Institution shall submit an annual or special report to the Council by compiling and analyzing the freedom of information implementation reports sent to it by Information Officers pursuant to this Proclamation, as well as gaps identified through its own supervision and monitoring.

2/ A special report submitted pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall include:

a) the full name and address of the public body, head of public body and the Information Officer who have refused to implement freedom of information provisions or the recommendations and decisions issued by the Institution;

b) the specific matter or freedom of information violation that triggered the report, and the recommendation or decision that was provided to the public body;

c) any harm caused to public or individual rights and interests as a result of the matter that triggered the report;

d) the written or oral response and justifications provided by the public body regarding the violation of freedom of information provisions or the Institution's recommendation;

ሠ) እንደአስፈላጊነቱ ሌሎች ጉዳዮች፤

ረ) በምክር ቤቱ በኩል ሊወሰድ የሚችል አማራጭ የተጠያቂነት አሰራር የሚይዝ ይሆናል።

ክፍል ስድስት

ቅሬታ እና ይግባኝ አቀራረብ

፵፯. ቅሬታ አቀራረብ እና ምላሽ አሰጣጥ ሥርዓት

፩/ በዚህ አዋጅ በተለየ ሁኔታ ካልተደነገገ በስተቀር በመረጃ ኃላፊ ውሳኔ ወይም በአዋጁ ድንጋጌ አፈጻጸም ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔ በደረሰው በ፴ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለበላይ ኃላፊ ቅሬታ ማቅረብ ይችላል። አመልካች ለበላይ ኃላፊ ቅሬታ ስለማቅረቡ ማረጋገጫ በመረጃ ኃላፊ ይሰጠዋል።

፪/ አመልካች ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ቅሬታ በጊዜው ማቅረብ አለመቻሉን ማስረዳት ከቻለ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተወሰነው ጊዜ ቢያልፍም ቅሬታ ማቅረብ ይችላል።

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የበላይ ኃላፊ፦

ሀ) ቅሬታው አስቸኳይ የመረጃ ጥያቄ ከሆነ ቅሬታ ከቀረበበት በ፵፰ ሰዓት፤

e) other matters as may be necessary;

f) alternative accountability mechanisms that may be taken by the Council.

PART SIX

PROCEDURES FOR COMPLAINTS AND APPEALS

47. Grievance Procedure and Response System

1/ Unless otherwise provided in this Proclamation, an applicant who is dissatisfied with a decision of the Information Officer or the implementation of the provisions of this Proclamation may lodge a complaint with the Head of the body within 20 consecutive days from the receipt of the decision. The Information Officer shall provide the applicant with an acknowledgment of the submission of the complaint to the Head.

2/ If the applicant can demonstrate that they were unable to submit the complaint on time due to force majeure, the complaint may be accepted even after the expiry of the period specified in Sub-Article (1) of this Article.

3/ The Head to whom a complaint is submitted pursuant to Sub-Articles (1) and (2) of this Article shall:

a) if the complaint concerns an urgent information request, render a final decision within 48 hours of the submission of the complaint;

ለ) ቅሬታው አስቸኳይ ባልሆነ መደበኛ የመረጃ ጥያቄ ከሆነ ቅሬታ ከቀረበበት በ፲ የሥራ ቀናት፤ ወይም

b) if the complaint concerns a regular non-urgent information request, render a final decision within 10 working days of the submission of the complaint; or

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) ፊደል ተራ (ሀ) እና (ለ) ባልተሸፈነና በሌላ የአዋጁ ድንጋጌ አፈጻጸም ላይ ቅሬታ በቀረበ ጊዜ ቅሬታ ከቀረበበት በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ የመጨረሻ ውሳኔ በመስጠት የውሳኔውን ግልባጭ ለቅሬታ አቅራቢ መሰጠት አለበት፡፡

c) if the complaint concerns the implementation of other provisions of the Proclamation not covered under paragraphs (a) and (b), render a final decision within 15 working days of the submission of the complaint and provide a copy of the decision to the complainant.

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሰረት በጊዜ ገደቡ ውሳኔ አለመስጠት በመረጃ ኃላፊ የተሰጠን ውሳኔ እንደመቀበል ይቆጠራል፡፡

4/ Failure to render a decision within the time limits specified in Sub-Article (3) of this Article shall be deemed as an affirmation of the decision made by the Information Officer.

፵፰. <u>አስተዳደራዊ ይግባኝ አቀራረብ</u>

48. <u>Submission of Administrative Appeals</u>

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፯ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) መሰረት በበላይ ኃላፊ በተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች ውሳኔ በደረሰው በ፳ ቀናት ውስጥ ለዋና ዕንባ ጠባቂ አስተዳደራዊ ይግባኝ በጽሑፍ ማቅረብ ይችላል፡፡

1/ An applicant dissatisfied with the final decision rendered by the Head pursuant to Article 47 Sub-Articles (3) and (4) may lodge an administrative appeal in writing to the Chief Ombudsman within 20 days of the receipt of the decision.

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአስቸኳይ የመረጃ ጥያቄ በመረጃ ኃላፊ በተሰጠ ውሳኔ ቅር የተሰኘ አመልካች በቀጥታ ለዋና ዕንባ ጠባቂ አስተዳደራዊ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፡፡

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, an applicant dissatisfied with a decision rendered by an Information Officer regarding an urgent information request may lodge an administrative appeal directly to the Chief Ombudsman.

፫/ ዋና ዕንባ ጠባቂ የቀረበው አስተዳደራዊ ይግባኝ አስቸኳይ የመረጃ ጥያቄ ከሆነ ይግባኝ ከቀረበበት በ፵፰ ሰዓት ውስጥ፤ አስቸኳይ የመረጃ ጥያቄ ያልሆነ ሌላ ጉዳይ ከሆነ በ፳ የሥራ ቀናት ውስጥ ተገቢውን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ መስጠት አለበት።

3/ The Chief Ombudsman shall render an appropriate decision or order within 48 hours if the administrative appeal concerns an urgent information request, or within 20 working days for any other matter.

፵፱. <u>አስተዳደራዊ ይግባኝ ስለሚቀርብበት ጉዳይ</u>

ለዋና ዕንባ ጠባቂ የሚቀርብ የበላይ ኃላፊ ውሳኔና አስተዳደራዊ ይግባኙ

ሀ) የመረጃ ክልከላ ውሳኔ፤

ለ) የተረጋገጠ ትክክለኛ ግልባጭ ክልከላ፤

ሐ) በተዘጋጀበት ቋንቋ ወይም ቅርጽ መረጃ አለመስጠት፤

መ) ለመረጃ ጠያቂ በጊዜ ገደቡ ምላሽ አለመስጠት፤

ሠ) የሦስተኛ ወገንን መረጃ ለመረጃ ጠያቂ የመስጠት ውሳኔ፤

ረ) የመረጃ ኃላፊ ወይም ባለሙያ አለመመደብ፤

ሰ) ለመረጃ ጠያቂ እገዛ ወይም ድጋፍ አለማድረግ፤

ሸ) የተጋነነ የመረጃ ክፍያ ውሳኔ፤

ቀ) የሕዝብ ጥቅም መረጃ አትሞ አለማሰራጨት፤ ወይም

በ) ለተመረጠ ወይም ለተወሰነ መገናኛ ብዙኃን ብቻ መረጃ የመስጠት ውሳኔ ወይም ድርጊት ያካትታል።

49. <u>Grounds for Administrative Appeal</u>

Administrative appeals to the Chief Ombudsman against a decision of the Head may be lodged on the following grounds:

a) a decision to refuse access to information;

b) a refusal to provide a certified true copy;

c) failure to provide information in the requested language or format;

d) failure to respond to an information requester within the specified time limit;

e) a decision to disclose a third party's information to a requester;

f) failure to designate an Information Officer or expert;

g) failure to provide assistance or support to an information requester;

h) a decision to charge excessive fees for information;

i) failure to publish and disseminate public interest information; or

j) a decision or act of providing information only to selected or specific mass media.

፶. ውሳኔ እና ትዕዛዝ አሰጣጥ

፩/ ዋና ዕንባ ጠባቂ በዚህ አዋጅ መሰረት የአስተዳደር ይግባኝ ሲቀርብለት፡

ሀ) ጉዳዩን በድርድር ወይም በስምምነት እልባት መስጠት፤

ለ) ማንኛውንም ሰው ከተቋሙ ፊት እንዲቀርብ መጥሪያ መላክ፤

ሐ) ለአስተዳደር ይግባኝ ምርመራ ተዛማጅነት ያለው ሰነድ ወይም ማስረጃ እንዲቀርብ ማዘዝ፤

መ) የተከለከለን መረጃ ወይም ሰነድ አስቀርቦ ሚስጢራዊነቱን በጠበቀ መልኩ የመመርመር ሥልጣን አለው፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ዋና ዕንባ ጠባቂ የቀረበውን የአስተዳደር ይግባኝ በመመርመር፡

ሀ) የበላይ ኃላፊ ወይም የመረጃ ኃላፊ ውሳኔ ማጽናት፤

ለ) ተቀባይነት ያገኘን ወይም የተጠየቀን የመረጃ ማግኛ ዓይነት መለወጥ፤

ሐ) የበላይ ኃላፊ ወይም የመረጃ ኃላፊ ውሳኔ በመተው አዲስ ውሳኔ መስጠት፤

መ) የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ግዴታ በተወሰነ የጊዜ ገደብ ውስጥ እንዲወጣ ማሳሰብ ወይም ማዘዝ፤

50. Decision-making and Issuance of Orders

1/ When an administrative appeal is submitted to the Chief Ombudsman pursuant to this Proclamation, he shall have the power to:

a) resolve the matter through negotiation or conciliation;

b) summon any person to appear before the Institution;

c) order the production of documents or evidence relevant to the investigation of the administrative appeal;

d) summon and examine prohibited information or documents while maintaining their confidentiality.

2/ Without prejudice to the provisions of Sub-Article (1) of this Article, the Chief Ombudsman, upon examining the administrative appeal, may:

a) affirm the decision of the Head or the Information Officer;

b) change the requested or approved form of access to information;

c) set aside the decision of the Head or the Information Officer and render a new decision;

d) warn or order a public body or a private organization to fulfill its obligations under this Proclamation within a specified timeframe;

ሠ) ግዴታውን ባልተወጣ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት የበላይ ኃላፊ ወይም የመረጃ ኃላፊ ላይ አስተዳደራዊ እርምጃ መወሰን፤ ወይም

ረ) አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ስልታዊ ምርመራ እንዲደረግ ትዕዛዝ ሊሰጥ ይችላል።

፫/ የስልታዊ ምርመራ ዝርዝር ተቋሙ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

e) decide on administrative measures against the Head or Information Officer of the public body or private organization who failed to fulfill their obligations; or

f) order a systemic investigation where necessary.

3/ The details regarding systemic investigations shall be determined by a Directive to be issued by the Institution.

፶፩. <u>አስተዳደራዊ እርምጃ</u>

፩/ ዋና ዕንባ ጠባቂ የመረጃ ነጻነት አፈጻጸም ቁጥጥርና ክትትል ግኝት ወይም አስተዳደራዊ ይግባኝ ምርመራ ውጤት መሰረት በማድረግ በበላይ ኃላፊ ወይም በመረጃ ኃላፊ ላይ እንደአግባብነቱ የሚከተሉትን አስተዳደራዊ እርምጃዎች በየደረጃው ሊወስድ ይችላል፦

ሀ) የጽሁፍ ማስጠንቀቂያ፤

ለ) ለምክር ቤት ልዩ ሪፖርት ማቅረብ፤ ወይም

ሐ) በመገናኛ ብዙኃን ማጋለጥ።

51. <u>Administrative Measures</u>

1/ Based on the findings of freedom of information implementation monitoring and supervision, or the results of an administrative appeal investigation, the Chief Ombudsman may take the following administrative measures, as appropriate, against the Head or Information Officer:

a) written warning;

b) submission of a special report; or

c) public exposure through the mass media.

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ፊደል ተራ (ሀ) መሰረት የሚሰጥ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ፦

ሀ) ማስጠንቀቂያ መስጠት ያስፈለገበትን ምክንያት፤

ለ) ሊወሰድ ስለሚገባው የማስተካከያ እርምጃ ዓይነት፤ እና

ሐ) የማስተካከያ እርምጃው ተፈጻሚነት የጊዜ ገደብ የሚገልጽ ሆኖ ለሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወይም የመረጃ ኃላፊ መድረስ ይኖርበታል።

2/ A written warning issued pursuant to Paragraph (a) of Sub-Article (1) of this Article shall:

a) state the reasons for issuing the warning;

b) specify the type of corrective measure to be taken; and

c) specify the time limit for the implementation of the corrective measure; and it shall be delivered to the concerned Head or Information Officer.

፫/ የጽሑፍ ማስጠንቀቂያ ከመሰጠቱ በፊት ጉዳዩ የሚመለከተው የበላይ ኃላፊ ወይም የመረጃ ኃላፊ ለአስተዳደራዊ እርምጃው መነሻ በሆነው ጉዳዩ ላይ ያለውን ምላሽ በጽሁፍ ወይም በአካል እንዲያቀርብና አስተያየት እንዲሰጥ እድል ሊሰጠው ይገባል፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የሚወሰን አስተዳደራዊ እርምጃ የማስተካከያ እርምጃ ውሳኔን፣ ትዕዛዝ ወይም ምክረ ሐሳብ ተፈጻሚነት አያስቀርም፡፡

፭/ አስተዳደራዊ ይግባኝ ማቅረብ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ አዋጅ ውስጥ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ለመረጃ ጠያቂ ምንም ዓይነት ምላሽ አለመስጠት ጉዳዩ በሚመለከተው የመረጃ ኃላፊ፣ የበላይ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ላይ ተቋሙ አስተዳደራዊ እርምጃ ሊወሰድ ይችላል፡፡

፶፪. <u>የውሳኔ አፈጻጸም</u>

፩/ የቅሬታ አቅራቢን አቤቱታ በመቀበል በበላይ ኃላፊ የተሰጠን የመጨረሻ ውሳኔ የማስፈጸም ኃላፊነት የመረጃ ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪/ የመንግሥት አካል ወይም የግል ድርጅት ዋና ዕንባ ጠባቂ የሰጠው ውሳኔ አስቸኳይ መረጃን የሚመለከት ከሆነ ውሳኔው በደረሰው በ፳፬ ሰዓት ወይም አስቸኳይ ያልሆነ መረጃ የሚመለከት ከሆነ ደግሞ ውሳኔው በደረሰው በ፲ ተከታታይ ቀናት ውስጥ መፈጸም አለበት፡፡

3/ Before a written warning is issued, the concerned Head or Information Officer shall be given the opportunity to provide a written or oral response and comments on the matter serving as the basis for the administrative measure.

4/ An administrative measure decided under Sub-Article (1) of this Article shall not exempt from the requirement to implement the corrective action, order, or recommendation.

5/ Without prejudice to administrative appeal, the institution may take administrative measures against the concerned information officer, head, or employee who fails to respond to the information requester within the time limit stipulated in this Proclamation.

52. <u>Execution of Decisions</u>

1/ The Information Officer shall be responsible for executing the final decision rendered by the Head in favor of a complainant.

2/ A public body or a private organization shall execute a decision rendered by the Chief Ombudsman within 24 hours of receipt if it concerns urgent information, or within 10 consecutive days if it concerns non-urgent information.

፫/ የዋና ዕንባ ጠባቂ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ አልተፈጸመልኝም በማለት የውሳኔው ተጠቃሚ ሲያመለክት ዋና ዕንባ ጠባቂ ውሳኔውን ወይም ትዕዛዙን እንዲያስፈጽምለት ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ወይም እንደአግባቡ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይመራል።

3/ Where a beneficiary of a decision notifies the Chief Ombudsman that a decision or order has not been executed within the time limits specified in Sub-Article (2) of this Article, the Chief Ombudsman shall refer the matter to the Federal High Court or the appropriate Regional Supreme Court to ensure the execution of the decision or order.

፶፫. <u>ይግባኝ</u>

፩/ በዋና ዕንባ ጠባቂ ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ወገን ጉዳዩ የፌደራል መንግሥት አካልን ወይም በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ የሚገኝ ወይም በፌደራል ደረጃ የተመዘገበን የግል ድርጅት የሚመለከት ከሆነ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት፤ የክልል መንግሥት አካልን ወይም በክልል ደረጃ የሚገኝ የግል ድርጅትን የሚመለከት ከሆነ ደግሞ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ውሳኔ በተሰጠ በ፳ ቀናት ውስጥ ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

53. <u>Appeal</u>

1/ Any party aggrieved by the decision or order of the Chief Ombudsman may lodge an appeal within 20 days from the date the decision was rendered to: the Federal High Court, if the case concerns a federal government organ or a private organization located in Addis Ababa or Dire Dawa or registered at the federal level; or to the Regional Supreme Court, if the case concerns a regional government organ or a regional-level private organization.

፪/ ይግባኝ የቀረበለት ፍርድ ቤት እንደአግባብነቱ ሚስጥራዊነቱን በጠበቀ መልኩ ይግባኙን በመመርመር ይግባኝ ከቀረበበት በ፴ የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

2/ The court to which an appeal is submitted shall examine the appeal while maintaining confidentiality, as appropriate, and shall render a decision within 30 working days of the submission of the appeal.

ክፍል ሰባት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፶፬. የወንጀል ቅጣት

፩/ በዚህ አዋጅ የተረጋገጠን የመረጃ ነጻነት ለመጣስ በማሰብ ሆነ ብሎ መረጃ ወይም ሰነድ፦

ሀ) ያጠፋ፣ ያበላሸ፣ የቀየረ፣ የደለዘ፤ የደበቀ ወይም ያፋለሰ

ለ) በተንኮል የከለከለ ወይም ሐሰተኛ ሰነድ የሰራ፤ ወይም

ሐ) ሙስናን ወይም ሌላ ሕገወጥ አሰራርን፣ የስራ አፈጻጸም ብቃት ጉድለትን ወይም የግለሰብ ወይም የመንግስት አካል ወይም የድርጅት ቅሌት ለመሸፈን መረጃ ወይም ሰነድ በሚስጢር እንዲያዝ ያደረገ የወንጀል ጥፋቱ በፍርድ የተረጋገጠበት የበላይ ኃላፊ፣ የመረጃ ኃላፊ ወይም ይህንን ያዘዘ ሌላ ኃላፊ 5 (አምስት) ዓመት በማይበልጥ እስራት ወይም በመቶ ሺህ ብር የገንዘብ ቅጣት ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ ቢኖርም፦

ሀ) ሆን ብሎ የተሳሳተ ወይም ትክክለኛ ያልሆነ መረጃ ወይም ሰነድ ለመረጃ ጠያቂ የሰጠ፤

ለ) በተቋሙ የተሰጠን ውሳኔ ወይም ትዕዛዝ ያለበቂ ምክንያት ያልፈጸመ፤

PART SEVEN

MISCELLANEOUS PROVISIONS

54. Criminal Penalty

1/ Any head, information officer, or person who, with intent to infringe access to information enshrined in this proclamation:

a) Destroys, damages, alters, conceals or erases a record;

b) Falsifies or makes a false record; or

c) Keeps or commands keeping any record confidential to cover up corruption, other illegal practices, incompetency, or scandal of individual, public body or organization commits an offence and liable on conviction to imprisonment for a term not exceeding Five years, or a fine 100,000 ETB, or both.

2/ Any public or private body head , information officer, or an employee who:-

a) knowingly discloses false or inaccurate information to a requester;

b) fails to execute a decision or order rendered by the Institution or

ሐ) በዚህ አዋጅ በተደነገገው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከአንድ ጊዜ በላይ በተደጋጋሚ ለመረጃ ጠያቂዎች ምላሽ ያልሰጠ የበላይ ኃላፊ የመረጃ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ጥፋቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ እንደ ጥፋቱ ክብደት ሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከ25,000 (ሃያ አምስት ሺህ) ብር በማያንስ ሆኖም 100,000 (አንድ መቶ ሺህ) ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

c) declines repeatedly responding to information requesters within the time limit provided under this Proclamation commits an offence and liable on conviction to a fine not less than Twenty-Five Thousand but not more than One Hundred Thousand Ethiopian Birr or to imprisonment for the term not exceeding Three years, or both.

፫/ ማንኛውም፦

3/ Any information officer, head, or employee who:

ሀ) የመረጃ ጥያቄን ለመቀበል ፈቃደኛ ያልሆነ፤

a) declines to accept a request for information;

ለ) መረጃ ወይም ሰነድ አትሞ የማውጣት ግዴታ ያልተወጣ፤

b) fails to publish and disseminate public interest information as per this proclamation;

ሐ) በቃል የቀረበን የመረጃ ጥያቄ በመረጃ መጠየቂያ ቅጽ ላይ ለመሙላት ፍቃደኛ ያልሆነ ወይም ግልባጩን ለመረጃ ጠያቂ ያልሰጠ፤

c) refuses to assist a requester who unable to write to reduce the oral request to writing in the prescribed form and provide a copy to the applicant;

መ) አካል ጉዳተኛ ሊነበብ፣ ሊታይ ወይም ሊደመጥ በሚችል አግባብ መረጃ ወይም ሰነድ ተደራሽ ለማድረግ ምክንያታዊ እርምጃ የመውሰድ ግዴታ ያልተወጣ፤ ወይም

d) fails to comply with the duty to take reasonable steps to make information available in a form that is capable of being read, viewed or heard by a requester with disability in accordance with this proclamation; or

ሠ) እያወቀ ሐሰተኛ ወይም የተዛባ መረጃ ወይም ሰነድ ለተቋሙ የሰጠ የበላይ ኃላፊ፣ የመረጃ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ጥፋቱ በፍርድ ቤት ሲረጋገጥ እንደአግባብነቱ አንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ) እስከ 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ወይም በሁለቱም ይቀጣል።

e) knowingly provides false or incorrect information to the Institution commits an offence and liable on conviction to imprisonment for a term not exceeding one year, or to a fine not less than 25,000 ETB but not more than 50,000 ETB, or both.

፬/ ሆን ብሎ በዚህ አዋጅ ውስጥ በግልጽ የተደነገገን ሌላ ግዴታ ወይም የመተባበር ግዴታ አለመወጣት በፍርድ ቤት ጥፋቱ የተረጋገጠበት የበላይ ኃላፊ፣ የመረጃ ኃላፊ ወይም ሰራተኛ ከብር 25,000 (ሃያ አምስት ሺህ) እስከ 50,000 (ሃምሳ ሺህ) ብር በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

4/ Any head, information officer, or employee who fails to comply with any other obligation that explicitly provided under this Proclamation commits an offence and liable on conviction to a fine not less than 25,000 ETB but not more than 50,000 ETB.

፶፭. ከተጠያቂነት ነጻ መሆን

55. Exemption from Liability

፩/ በዚህ አዋጅ ውስጥ የተመለከቱትን ግዴታዎችና ኃላፊነቶች በቅን ልቦና ለመፈጸም በተደረገ ማንኛውም ዓይነት ድርጊት የመረጃ ኃላፊ ወይም ባለሙያ እና መረጃውን በቅን ልቦና ያሰራጨ የመገናኛ ብዙኃን ባለሙያ ከወንጀል እና አስተዳደራዊ ተጠያቂነት ነጻ ነው።

1/ Any information officer or employee, or media professional who disseminates information in good faith shall be immune from criminal and administrative liability for any act done in good faith to discharge the duties and responsibilities specified in this proclamation.

፪/ ማንኛውም ግለሰብ ወይም መገናኛ ብዙኃን የሕግ ወይም የሥራ ግዴታን በመተላለፍ ሆን ብሎ ጥፋትን ወይም የሕዝብ ጤንነትን፣ ደኅንነትን ወይም ካባቢያዊ ደኅንነትን ወይም ጎጂ የሆነ ከባድ አደጋን የሚመለከት መረጃ በመግለጹ ወይም ይፋ በማድረጉ ለሕጋዊ ወይም አስተዳደራዊ ቅጣቶች የማይዳርገው መረጃው፦

2/ No individual or media professional shall be subject to legal or administrative penalties for intentionally disclosing or publicizing information regarding a violation of the law, a breach of duty, or a serious threat to public health, safety, or the environment, provided they acted in good faith with a reasonable belief that the information reveals:

ሀ) አግባብነት ባለው ሕግ ጥፋት ተብሎ የተፈረጀ ተግባርን፤

ለ) የሕዝብ ጤንነትን፣ ደኅንነትን ወይም ከባቢያዊ ደኅንነትን ጎጂ የሆነ ከባድ አደጋን፤

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) የተመለከተውን ጥፋት ወይም ጎጂ የሆነ ከባድ አደጋ ይፋ በማድረግ ለበቀል እርምጃ መዳረግን፤ ወይም

መ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ተራ ፊደል (ሀ) እና (ለ) የተመለከተውን ጥፋት ወይም ጎጂ የሆነ ከባድ አደጋ ሆን ብሎ መደበቅን ሊያሳይ ይችላል የሚል ምክንያታዊ እምነት በመያዝ ድርጊቱን በቅን ልቦና የፈጸመው እንደሆነ ነው።

a) an act defined as an offense under relevant laws;

b) a serious danger to public health, safety, or the safety of the environment;

c) retaliatory measures taken against someone for disclosing the offenses or dangers mentioned in Sub-Article (2) Paragraph (a) and (b) of this Article; or

d) the intentional concealment of the offenses or dangers mentioned in Sub-Article (2) Paragraph (a) and (b) of this Article.

፫/ ለዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) አላማ ከግለሰብ ድርጊት ጋር ተያያዥነት ቢኖረውም ባይኖረውም ጥፋት ማለት የወንጀል ድርጊት፣ የሕግ ግዴታ መተላለፍ፣ ፍትህ ማዛባት፣ ሙስና፣ ማጭበርበር፣ በሥልጣን ያለአግባብ መጠቀም፣ የሰብአዊ መብት ጥሰት፣ ዓለም አቀፍ የጦርነት ሕግ ጥሰት ወይም በሕዝብ ሃብት ላይ የሚፈጸም ብክነት ማለት ነው።

3/ For the purposes of Sub-Article (2), an offense includes criminal acts, violations of legal obligations, miscarriage of justice, corruption, fraud, abuse of power, human rights violations, violations of international humanitarian law, or waste of public resources, regardless of whether it is linked to an individual's actions.

፬/ ጥፋትን ወይም ጎጂ የሆነ ከባድ አደጋን የተመለከተ መረጃ በመግለጹ ወይም ይፋ በማድረጉ አስተዳደራዊ ወይም ሕጋዊ ቅጣት የተላለፈበት ሰው ውሳኔውን ካወቀበት ቀን ጀምሮ ባሉት ፴ ቀናት ውስጥ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፫ አግባብ ለፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል።

4/ Any person who is subjected to an administrative or legal penalty for disclosing information regarding an offense or a serious danger may lodge an appeal to the court in accordance with Article 53 of this Proclamation within 30 days of becoming aware of the decision.

፶፮. <u>የተዛባ መረጃ ሥርጭት</u>

፩/ በዚህ አዋጅ መሰረት ከመንግሥት አካል ወይም ከግል ድርጅት የተገኘ መረጃ ወይም ሰነድ እውነተኛና ትክክለኛ መረጃ ወይም ሰነድ ነው ተብሎ ይገመታል።

፪/ በዚህ አዋጅ መሰረት ከመንግሥት አካል ወይም ከግል ድርጅት የተገኘን መረጃ ወይም ሰነድ በማዛባት መጠቀም ወይም ማሰራጨት የተከለከለ ነው።

፫/ የዚህን አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ የጣሰ ማንኛውም ሰው ከአንድ ዓመት በማያንስ ነገር ግን ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ጽኑ እሥራት ይቀጣል።

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) ድንጋጌ ቢኖርም በዚህ አዋጅ መሰረት ከመንግሥት አካል ወይም ከግል ድርጅት በተገኘ መረጃ ወይም ሰነድ ውስጥ የተካተተን የተዛባ ወይም ሐሰተኛ መረጃ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ወይም በሦስተኛ ወገን እንዲታተም ማድረግ ስርጭቱ ወይም ሕትመቱ በክፉ ልቦና የተደረገ ስለመሆኑ ካልተረጋገጠ በስተቀር መረጃውን ይፋ ያደረገ አካል ልዩ መብት ይኖረዋል።

፭/ ሐሰተኛ ወይም የተዛባ መረጃ ስርጭት በመገናኛ ብዙኃን በተፈጸመ ጊዜ በፍርድ ቤት የጥፋተኝነት ውሳኔ ከመሰጠቱ በፊት ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ለምርመራ ወይም ለሌላ ምክንያት ጋዜጠኛን፣ ዋና አዘጋጅን ወይም ከጉዳዩ ጋር በተያያዘ ሌላ ሰው ለእስራት መዳረግ የተከለከለ ነው።

56. <u>Distribution of Distorted Information</u>

1/ Information or documents obtained from a public body or a private organization under this Proclamation shall be presumed to be authentic and accurate.

2/ It is prohibited to use or disseminate information or documents obtained under this Proclamation in a distorted manner.

3/ Any person who violates the provisions of Sub-Article (2) of this Article shall be punished with rigorous imprisonment of not less than One year and not more than Two years.

4/ Notwithstanding Sub-Article (2), a party that discloses distorted or false information contained within a document obtained from a public body or private organization, or allows it to be published by a third party, shall have a privilege unless it is proven that the dissemination or publication was done in bad faith.

5/ When the dissemination of false or distorted information is committed through the mass media, it is prohibited to imprison a journalist, editor-in-chief, or any other person in connection with the case for investigation or any other reason prior to a court's guilty verdict.

፶፮. <u>ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን</u>

፩/ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈጸም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ ተቋሙ ይህን አዋጅ እና በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የሚወጣን ደንብ ለማስፈጸም የሚችሉ ልዩ ልዩ መመሪያዎች ያወጣል፡፡

57. <u>Power to Issue Regulations and Directives</u>

1/ The House of Peoples' Representatives may issue Regulations to implement this Proclamation.

2/ The Institution shall issue various Directives to implement this Proclamation and the Regulations issued by the House of Peoples' Representatives.

፶፯. <u>የመሸጋገሪያ ድንጋጌ</u>

በመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ ነጻነት አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፯/፪ሺ ክፍል ሦስት ድንጋጌ መሠረት በመታየት ላይ ያለ የመረጃ ጥያቄ፣ ቅሬታ፣ አስተዳደራዊ ይግባኝ ወይም ይግባኝ በነባሩ አዋጅ መሠረት እልባት እንዲያገኝ ይደረጋል፡፡

58. <u>Transitional Provision</u>

Any information request, grievance, administrative appeal, or court appeal currently pending under the provisions of Part Three of the Freedom of the Mass Media and Access to Information Proclamation No. 590/2008 shall be resolved in accordance with the old Proclamation.

፶፰. <u>የተሻሩና ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች</u>

፩/ የመገናኛ ብዙኃንና የመረጃ ነጻነት አዋጅ ቁጥር ፭፻፺፯/፪ሺ ክፍል ሦስት ድንጋጌዎች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

፪/ የዚህን አዋጅ ድንጋጌ የሚቃረን ማንኛውም ሕግ፣ ትዕዛዝ ወይም አሰራር በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

59. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>

1/ The provisions of Part Three of the Freedom of the Mass Media and Access to Information Proclamation No. 590/2008 are hereby repealed.

2/ Any law, order, or practice that is inconsistent with this Proclamation shall not be applicable to matters covered under this Proclamation.

፷. <u>አዋጁ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ ነሐሴ ፳ ቀን ፪ሺ፲፰ ዓ.ም

ታዬ አጽቀሥላሴ

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

60. <u>Effective Date</u>

This Proclamation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazette.

Done at Addis Ababa, On this 26th day of August, 2026

TAYE ATSKESELASSIE

PRESIDENT OF THE FEDRAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA